

# መዝሙረ ጸሎት

ከኢሳይያስ ዓለሜ

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት

በ፫ ዓይነት ድምፅ (ዜማ)

ተዘጋጀ።

ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ

ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ ።

መጀመሪያ በ፲፱፻፹፯ ዓ ም ሐምሌ ፲፯ } ታተመ ።
ሁለተኛ እንደገና ተሻሽሎ በ፲፱፻፹፱ ዓ ም

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## ግርማዊ ሆይ !

ሕዝብ በሚያውቀው አማርኛ እየዘመሩ መጸለይና ፈጣሪን መለመን ለሀገራችን የመጀመሪያ ጊዜ የሆነችውን ይህችን ትንሽ መዝሙረ ጸሎት ለግርማዊነትዎ ሳበረክት አነሣስቶ ያስጀመረኝ እግዚአብሔርን በማመስገን ነው ።

የግርማዊነትዎንም ዘመነ መንግሥት በሆሣዕና መስዬ እናገራለሁ ። ይህንንም ያልሁበት ምክንያት በሆሣዕና ጊዜ የቢታንያ አዕሩግና ሕፃናት « ሆሣዕና በአርያም ቡሩክ ዘይመጽዕ በስመ እግዚአብሔር » እያሉ እንዳመሰገኑ ፤ እኛም የኢትዮጵያ ሕፃናት ፈጣሪያችንን በአማርኛ መዝሙር ለማመስገን ችለናል ።

## ግርማዊ ሆይ !

ይህች አጭር መዝሙረ ጸሎት ከ፲፱፻፵፯ ዓ. ም እስከ ዛሬ ድረስ በቅድስት ሥላሴ መ|ት|ቤት የአዲስ አበባ ተማሪዎች እየተሰበሰቡ ሲዘምሩባት ቆይተው ፀ፵፫ ዓ ም በየጠቅላይ ግዛቶቹ ተዳርሳለች ።

ደግሞም ከግርማዊነትዎ ረድኤት ጋር አውታረ ልቡናየን ከማጽናናታቸው በላይ እንደ አባትነታቸው እየ መከሩ እንደ በላይነታቸውም እያዘዙ ዛሬ ከግርማዊነ ትዎ ፊት ለመድረስ ያበቁኝ ባለሥልጣኖች በ፮ኛው ገጽ ላይ መጽሐፍዋን ሲመረምሩ ይታያሉ ።

ከዚህ በላይ ግን በአፄ ገብረ መስቀል አድሮ የቅዱስ ያሬድን ጸዋትወ ዜማዎች በሙሉ ለኢትዮጵያ ያደረሰ እግዚአብሔር ዛሬም ከግርማዊነትዎ ጋር ስለተገኘልኝ የአምልኮት ምስጋናየን አቀርብለታለሁ ።

አገልጋይዎ

ኢሳይያስ ዓለሜ



" ትውልደ ጻድቃን ይትበረኩ "

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ ሥ. ከተባረከ ንጉሣዊ ቤተ ሰባቸው ጋር ።

www.ethiopianorthodox.org



«ረአይኬ አባግዕየ»
ባስልዮስ ሊቀ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

## "ሀገሩን የሚወድ የታሪክ ጌታ ነው»"

ለሀገራችን የመጀመሪያ ጊዜ የሆነውን የአማርኛ መዝሙረ ጸሎት መጽሐፍ በ፫ት ዓይነት ድምፅ ( ዜማ ) ተዘጋጅቶ በደራሲው በኢሳይያስ ዓለሜ አቅራቢነት በተከበሩ ባለ ሥልጣኖች ሲመረመር ይታያል ። በዚህም መጽሐፍ በኢትዮጵያ ን. ኦ. መ. ኦርቶዶክሳዊት ( ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል መልእክተኞች ማኅበር ከ፲፱ ፻፵፯ ዓ ም — ፵፱ ዓ ም ተመርቶበት እንደገና ተሻሽሎ ታተመ ።

---





«ሀገሩን የሚወድ የታሪክ ጌታ ነው »

በመካከል የሐረሬ ጳጳስና የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት ዋና እንደራሴ ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ

በቀኝ ክቡር አቶ አካለ ወርቅ ሀብተ ወልድ ። በግራ አቶ አበበ ሥዩም

www.ethiopianorthodox.org

# መቅድም

መዝሙረ ጸሎት ። መዝሙር ማለት ያዘኑትን የሚ ያስደስት ፣ የተበሳጩትን የሚያረጋጋ ከመሆኑ በላይ የተ በተነ የሰውን ሀሳብ አንድ አድርጐ ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ የሚያገናኝ ነው ።

ይኸውም ሊታወቅ ክቡር ዳዊት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ በበገናው ሲደረድር መዝሙር ፵፮ ቍ ፮

ዘምሩ ለአምላክነ ዘምሩ ፣

ዘምሩ ለንጉሥነ ዘምሩ ፣

ማለቱ በመዝሙር አምላክን ማመስገን እንዲገባ ያስረዳል ። ፪ኛም ፺፪ ከ፩ - ፪ ልዑል ሆይ አንተን ማመስገ ንና ለስምህ መዘመር መልካም ነው ፣ ያለውን እናስታ ውስ ። ከዳዊት መዝሙር እሊህን ሁለት ጥቅሶች ብቻ መጻፈ ለማስታወሻ ያህል ነው እንጂ ዳዊት የተናገረው በሙሉ መዝሙር መሆኑ የተሰወረ አይደለም ።

ደግሞም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተ ልሔም ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ መላእክትና ሰው አንድ ሁነው ዘምረውለታል ፣ (ሉቃ ፪ - ፲፫ ።)

ስለዚህ መዝሙር የሰውን ሀሳብ ወደ እግዚአብ ሔር የሚመራ መሆኑ በዚሁ ይታወቃል ። ይህንንም መሠ ረት በማድረግ ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት ታስረው ሥቃይ ፀንቶባቸው ሳለ በመንፈቀ ሌሊት ተነሥተው ወደ አምላካቸው በመዝሙር በጸለዩ ጊዜ ከእሥራታቸው ተፈተዋል ፣ ከመከራውም ድነዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

በወህኒ ቤቱም የተደረገው መነዋወጥ ታላቅ ነበር ። (የሐዋርያት ሥራ ፲፮ (፳፭ - ፴፱) እንግዲህ እኛም የነሱ ተከታዮች ከሆነ ሥራችን ሥራቸውን ሀሳባችን ሀሳባቸውን መከተል በክርስቶስ ክርስቲያኖች ለሆነ ሁሉ ተገቢያችን መሆኑን ተገንዝቤ ፣ ለጊዜው ይህንን አጭር መዝሙረ ጸሎት ስጽፍ ከብሉይና ከሐዲስ እየጠቀስሁ ነው እንጂ ልብ ወለድ አለመሆኑን ሳስታውሳችሁ ምሥጢሩን እንጂ ጥሬ ንባቡን እንዳትመለከቱ ነው ።

ይኸውም የተደከመበት አጭር መዝሙረ ጸሎት የዜማው ስልት ለመሰንቆ አርጋኖንና (ለአርጋን) ለፒያኖ እንዲሁም ኖት ላላቸው የመዝሙር መሣሪያዎች ሁሉ ተስማሚ መሆኑን ለመዘመር አፍቃሪዎች አስገነዝባለሁ ።

መዝሙረ ጸሎት ምን ያህል ጥቅም እንደሚያሰጥ ከዚህ በታች ያሉት ጥቅሶች ከብዙ በጥቂቱ ያስረዳሉ ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩ | አሬ ዘፀ | ፲፭ ቊ ፩ | ፱ | » » | ፺፰ ፣ ፩ ፣ ፬ - ፭ |
| ፪ | አሬ ዘኊ | ፳፩ ፣ ፲፯ | ፲ | » » | ፺፪ ፣ ፩ - ፪ |
| ፫ | ዘካርያስ | ፩ ፣ ፳፰ | ፲፩ | ኢሳይያስ | ፲፪ ቊ ፪ |
| ፬ | ፪ኛ ሳሙኤል ፣ | ፳፪ | ፲፪ | » | ፳፬ ፣ ፲፯ |
| ፭ | የዳዊት መዝሙር | ፵ ፣ ፫ | ፲፫ | ሉቃ | ፩ ፣ ፵፯ |
| ፮ | » » | ፵፯ ፣ ፰ | ፲፬ | ኤፌ | ፭ ፣ ፲፱ |
| ፯ | » » | ፹፱ ፣ ፲፪ | ፲፭ | ቆላ | ፫ ፣ ፲፯ |
| ፰ | » » | ፻፲፰ ፣ ፲፬ | ፲፮ | ራዕይ | ፲፭ ፣ ፫ |

## የጳውሎስ መልክት ወደ ሮሜ ሰዎች

### ምዕራፍ ፲፪ ።

፩) መሥዋዕት አድርጉለት ሰውነታችሁን ፣ ቊ ፩
ሕያው ለሚሆነው ለቸር ፈጣሪያችን ።

፪) ብዬ በእግዚአብሔር ስማልዳችሁ ፣
በዕውቀት እንዲሆን መገዛታችሁ ።

፫) እንደተወደደ እንደተቀደሰ ፣
ይሁን ቁርባናችሁ ከሁሉም የባሰ ።

፬) ይህንንም ዓለም ሰዎች አትውደዱት ፣ ቊ ፪
ልባችሁን በዕውቀት ፈጥናችሁ አድሱት ።

፭) እግዚአብሔር አምላክ የሚወደውን ፣
በጎውን መርምሩ ያዙ ፍጹሙን ።

፮) ኩራትን ከናንተ ጣሉ ፈጽማችሁ ፣ ቊ ፫
በተሰጠኝ ጸጋ እነግራችኋለሁ ።

፯) ከትልቁ ኃጢአት ከዝሙት በስተቀር ፣
ሁሉም በሃይማኖት እንዳደለው ይኑር ።

፰) በሰውነታችን ብዙ አባሎች አሉ ፣ ቊ ፬
የተለያየ ነው ሥራቸው ለሁሉ ።

፱) እንዲሁም ሁላችን ብዙ ስንሆን ፣ ቊ ፭
ሁላችን አንድ አካል በክርስቶስ ነን ።

፲) የእግዚአብሔር ስጦታ ሀብቱ ልዩ ነው ፣ ቊ ፮
እንደ ሃይማኖቱ ይናገራል ሰው ። (ትንቢት)

www.ethiopianorthodox.org

፲፩) የሚያገለግልም ይትጋ በሥራው ፥ ሮሜ ፯
ደስ ብሎት ይመጽውት የሚሰጥም ሰው ።

፲፪) የሚሾምም ሁሉ በተሾመበት ፥ ሮሜ ፰
ደስ ብሎት ይሥራ በፍጹም ትጋት ።

፲፫) ፍቅራችሁም ይሁን ያለጥርጥር ፥ ሮሜ ፱
ክፉውን ትታችሁ በበጎ ነገር ።

፲፬) ወንድሞቻችሁን ውደዱ ሁላችሁ ፥ ሮሜ ፲
ደግሞም ተዛዘኑ እርስ በራሳችሁ ፥
( ትህትናን አሳዩ ለመምርቻችሁ ) ። ( አክብሯቸው )

፲፭) ቸል አትበሉ እናንተ ለሥራ ከመትጋት፥ሮሜ ፲፩
በነፍስ እንድትድኑ ከሁለተኛ ጥፋት ።

፲፮) መከራን ታግሷት ደስ ይበላችሁ ፥ ሮሜ ፲፪
ጸሎትም ጸልዩ በጣም ተግታችሁ ።

፲፯) ቅዱሳንን እርዱ ሁላችሁ ባንድነት ፥ ሮሜ ፲፫
እንግዳም መቀበል አዘውትሩ በውነት ።

፲፰) በጠላት ማሳደድ ብትወጡም ከሀገር ፥ ሮሜ ፲፬
እንዳትረግሙ ፥ ከመመረቅ በቀር ።

፲፱) ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ ፥ ሮሜ ፲፭
ከሚያዝኑትም ጋራ ይዘን ልባችሁ ፥



፳)ትዕቢትን እርቁ ከሰውነታችሁ ። ሮሜ ፲፮
ትህትናንም ያዙ ከበጎው ዓይታችሁ ፥ (ራሳችሁን አዋርዱ)

፳፩) አጥቂችሁን እኛ ሳትሉ እንደነሱ ፥ ሮሜ ፲፯
ለበደሏችሁም ክፉ አትመልሱ ።

፳፪) እናንት ወንድሞቼ ቢቻላችሁስ ፥ ሮሜ ፲፰
ወንድማማች ሁኑ በመንፈስ ቅዱስ ። (ከሁሉ ጋር)


፳፫) በቀልን እርሷት ቁጣንም ምምር ፥ ሮሜ ፲፱
እኔ እበቀላለሁ ብሏል እግዚአብሔር ።

፳፬) ሲራብም ሲጠማም ብትሰጥ ለጠላትህ ፥ ሮሜ ፳
የሳት ፍም በራሱ ትሰበስባለህ ።

፳፭) ክፉውን በክፉ ድል መንሣት አያሻም ፥
እንደተጻፈልህ ድል ንሣው በመልካም ።

ከዚህ በላይ የተጻፈው መዝሙር መነቃቀፍ እንዳ
ይኖር ያስረዳል ።

www.ethiopianorthodox.org




ደራሲው በመሰንቆ አርጋኖን (በኦርጋን) ላይ ሁኖ
ዜማውን ሲያሰማ ።

www.ethiopianorthodox.org

# መዝሙር

## ስለ ርዕሰ ዓውደ ዓመት ።

ቁ ፩ በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬ት ፣
ዮሐንስ ያሳያል ክብሩን ለፍጥረት ።
፪ የተፀደለ ሰይፍ በንጉሥ ሄሮድስ ፣
ላንተ ተሳለልህ ቅዱስ ዮሐንስ ፣
፫ የሚያወራርድ ነው ያንተውስ ስለት ፣
አይሰማም የሚሉ አሉ ሕፃናት ።
፬ እንግዲህ ዮሐንስ ስለትህን ተቀበል ፣
በሕፃናቱ ዘንድ በዝቶበታል ብደል ፤
( ውሀ ሲያጠጣቸው ቆፍሮ በመግደል ። )
፭ ትሕትና ተሰጠህ አንተ ዮሐንስ ፣
ራስህ በመላክ ስትመላለስ ።
( በማታውቀው አገር በመላኩ ንግሥ )
፮ ከዮሐንስ ቢያድር የተራበ ሥጋ ፣
በመላክ ደከመ ሁል ጊዜ እንደ ተጋ ፣
( ዓመተ ምሕረቱን ሕጉን ሳይዘነጋ ። )
፯ አንቺ ቤተ መቅደስ መላክ የምትወጅ ፣
ፍሬው ሃይማኖት ነው የምትልኪው ልጅ ።
፰ ለሃይማኖት ቢሞት ዮሐንስ በምር ፣
ሕፃናት መርምሩ ያገኘውን ክብር ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፱ ሃይማኖት ከምግባር ነፍስና ሥጋ ናት ፣
ምግባርን አትተው ሃይማኖት እንዳትሞት ።
፲ ነፍስ የተለየውን ሥጋ ተመልክተህ ፣
እንደርሱ እንዳትሆን መርምር አስተውለህ ።

ከሁን ጀምረው በጌታ የሚሞቱ ብፁዓን ናቸው ፣
መንፈስ ይላል አዎን ከድካማቸው ያርፋሉ ምግባ
ራቸውም ትከተላቸዋለች ( ራዕ ፲፬ ፲፫ )

## መዝሙር ፡ ፪

## ዘመስቀል ።

፩ ደሙን ያፈሰሰ ንጉሥ ክርስቶስ ፣
በዕፀ መስቀል ነው ካለው ሁሉ ቅርስ ።
፪ አንዲት ዕፀ መስቀል ብርሃን የምትሰጥ ፣
ስታበራ ታዩች በመቃብር ውስጥ ።
፫ ዛሬስ ዕፀ መስቀል በሌላ ሲፈርዴ ፣
ዓይን አውጣ ተባለ በሕሙማን ዘንድ ።
፬ መስቀል ኃይላችን ነው ለደከመን ሁሉ ፣
ኃይል የተሰጠነ ለእኛነው አትበሉ ።
፭ ማን ይመረምራል የመስቀልን ነገር ፣
እሱ በእንጨት ሲሄድ ሐንካሳንን በእግር ፣
( ሲያስሄዳቸው ዋለ በፈቀዱት አገር ። )



፯ አንተ የእንጨት መስቀል በደም ተገኘተህ ፣
አይሁድ ተቸገሩ በመቃብርህ ።
፰ እሌኒ ብትመጣ በከበደ ግርማ ፣
በጢስ ተመራበት በመስቀል ከተማ ።
፱ የመስቀል ከተማ ብርሃን የመላው ፣
በንግሥት እሌኒ ተሰማ ዜናው ።

## መዝሙር ፡ ፫

## ዘመነ ጽጌ ።

( ቁጥር ፳፰ ምዕራፍ ፮ኛ )

፩ በማቴዎስ ወንጌል ከታዘዘው ለእኛ ፣
ባለመጠራጠር ተመልክት ተክለኛ ።
፪ ከበቦቹ ጋራ የምትውል አንተ ነህ ፣
እንደነሱ ያለ ልብስም አላገኘህ ፣
( አንተም እንደነሱ አታስብ ለራስህ ። )
፫ ጥበብ የተሰጠው ሰሎሞን ንጉሥ ፣
እንደ አበቦች ያለ አለበሰም ልብስ ።
፬ ሰው በራሱ ሀሳብ እንዳያገኝ ዋጋ ፣
በዚህ ይታወቃል የክርስቶስ ጸጋ ።
፭ እነዚህ አበቦች ያላንዲት ሀሳብ ፣
ፍሬያቸው ያጠግባል ለተራበው ሕዝብ ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ሰው አሳቢ ቢሆን ሁል ጊዜ ለሥጋው ፣
እስከ ዕለተ ሞቱ ድካም ሆነ ዋጋው ።
፯ አሳቡን የጣለ በክርስቶስ ዘንድ ፣
ሲመገብ ይኖራል ሳይወጣ ሳይወርድ ።
፰ እንግዲህ ሁላችን እናስብ እሱን ፣
መጋቢ እንዲሰጠን መንፈስ ቅዱስን ፣
፱ ደግሞም መንፈስ ቅዱስ የሚመግበን ፣
እንደ ልባችን ነው እንወቅ ይህን ።
፲ ሰው የፈለገውን እንደ ልቡ ሲያገኝ ፣
ልቤን እንዳነፃ መንፈስ አስገደደኝ ።

## መዝሙር ፬

## ልደተ ክርስቶስ ።

፩ በረቂቅ ልደቱ ያገኘነው ጸጋ ፣
ካንድ ላይ አደሩ እሳትና ሥጋ ።
፪ እናንተ ሕፃናት በጣም ተደሰቱ ፣
ብርሃን ከተገኘ ዛሬ በልደቱ ።
፫ ሕፃናት እደጉ ከልደቱ ቤት ፣
ውሀ ሁኚልና ማርና ወተት ።
፬ ከበረት እንሂድ ሕፃናቱ ሁሉ ፣
አንበሳ ከላምጋር ይጫወታል አሉ ።
፭ የዓለም መድኃኒት የድንግል ፍሬሽ ፣
መዓዛው ሃይማኖት የማይበላሽ ።

## የዓለም መድኃኒት ።






www.ethiopianorthodox.org

፯ ሰማይና መሬት የማይወስኑት ፤
አምላክ ተወሰነ በጠባብ ደረት ።
፰ ዐነቢያት ያለው ድንግል ምሳሌሽ ፤
አንበሳ ወልደ አብ ገዳም አንቺ ነሽ ።
፱ ትንቢቱ ምሳሌው ዛሬ ሲያስረዳን ፤
ዕጣንና ከርቤ ወርቅም ካንቺ አዬን ።

በሌላ በማንም ደኅንነት የለምና በሰማይ ታች ለሰው የተሰጠ ይድንበት ዘንድ ከኢየሱስ ስም በቀር ሌላ ስም የለም ። (የሐዋ ፬ ፡ ፲፪ ።)

## መዝሙር ፳

## ጥምቀት በዮርዳኖስ

፩ ለምን ትሸሻለሽ አንቺ ዮርዳኖስ ፤
ወዳንቺ ሲመጣ የክብርሽ ንጉሥ ።
፪ የዲያብሎስ መዝገብ ከቤትሽ ቢጠፋ ፤
የመንግሥተ ሰማይ ክብራችን ተስፋፋ ።
፫ ባንዲት ዕፀ በለስ ያመጣው አዳም ፤
ተደምስሶ ቀረ የባርነት ስም ።
፬ እንግዲህ የማይ ልጅ አትሆንም ደሀ ፤
ከራስ በላይ ዋለ የዮርዳኖስ ውሀ ።
፭ ሥጋ የለበሰው የማርያም ልጅ ፤
ውሀውን ለወጠው በሚያረካ ጠጅ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፮ መንፈቅ የምትበልጠው ሕያው ክርስቶስ ፣
በጣም አክበረህ አንተ ዮሐንስ ።

፯ ልብስህ ጠጉር ቢሆን ምግብህም አንበጣ፣ (አንበጣ)
አንዳንት የከበረ ክየትም አይመጣ ።

፰ ያምላክነት ሥራ በጣም የረቀቀ ፣
በገሊላ አውራጃ በቃና ታወቀ ።

## መዝሙር ፯

## የክርስቶስ ጾምና ፈተና ።

፩ በ፬ኛው ምዕራፍ በማቴዎስ ውስጥ ፣
መድኃኒታችን ጾም ይታያል ሲሰጥ ።

፪ ሰው በእንጀራ ብቻ እንዳይኖር ተጽፏል ፣
በጣም እንጠብቅ የክርስቶስን ቃል ።

፫ ሰይጣን የፈተነው አምላካችንን
በፍቅረ ንዋይ ነው እንወቅ ይህን!።

፬ ይህን ያላወቀ ያልተማረ ሰው ፣
ለዚያ ክፉ ሰይጣን ማደሪያ ሆነው ።

፭ ክርስቶስ ቢሠራው የጾምን ሐውልት ፣
የይሁዳ ልጆች መጡ ሊያፈርሱት ።

፮ ምን ያለች ደግ ናት የክርስቶስ ዱር ፣
ሐውልቷ ቀናና የማይሰበር ።



፯ ጾም ጥናታችንን እንግዲህ እናጥና ፣
ፈተናው ታወቀ የማይቀር ነውና ።

፰. ሰይጣን ተሰደደ መፈተኑን ለቆ ፣
ፍጹም ጥናታችን ጾም መሆኗን አውቆ ።

፱. ይኸ ክፉ ሥጋ የሰይጣን ዘመድ ፣
አብሬ ካንተ ጋር ይላል ልሰደድ ።

የእግዚአብሔር ልጅ የሰይጣንን ሥራ ሊሽር ተገ ለጠ (፩ ዮሐ ፫ ፰) ሰይጣንን ተቋቋሙት ከላንተ ይሸ ሻል ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እሱም ወደላንተ ይቀር ባል ፣ ( ያዕቆብ ፬ ፯-፰

## መዝሙር ፰

## ሕይወት በመፃጉዕ

፩. በማርቆስ ወንጌል በሁለቱ ምዕራፍ ፣
የመፃጉዕን ታሪክ ተመልከት ሳትሰንፍ ።

፪. የመፃጉዕን ሕይወት የመከራት ጌታ ፣
ባልጋ እንዳትቀር ነው እንዳትሆን ወስላታ ።

፫. ባልጋማ ብትቀር እንዳልተመከረች ፣
ሕይወት ቤቷን አጥታ ትቀበር ነበረች ።

፬. መፃጉዕን ካልጋው ላይ ያስነሣው ንጉሥ ፣
ሥጋን አደረጋት የሕይወት መቅደስ ።

www.ethiopianorthodox.org

፭· ካ፲ኛው ቁጥር ብትመለከቱ ፣
ለሰው ልጅ ተሰጠ ሥልጣን ካንደበቱ ።
፮· በተሰጠን ሥልጣን እናስተምር በጣም ፣
ኃጢአትን አጥፍተን እንድናገኝ ሰላም ።
፯· መጣጥር ከንቱ ነው ሁል ጊዜ ለሥጋ ፣
ጾምን ካላወቅነ አትገኝም ጸጋ ።
፰· ባለ መጾም ሊያገኝ መንፈስ ቅዱስን ፣
ጸጋ ብሎ ጠራው አንድ ሰው ልጁን ።
፱· ትዕቢትን እናጥፋት ሁላችን በተራ ፣
መከራ እንዳትጥለን ከዲያብሎስ ጋራ ።
፲· ትዕቢት ለዲያብሎስ እኅቱ ስትሆን ፣
በጣም ጠንክራችሁ ጠብቋት ሰላምን ።
፲፩· ሰላምን ለማጥፋት ትዕቢት ብትነሣ ፣
ሰባብሮ ጣለልን የልደት አንበሳ ።

## መዝሙር ፰

## ሐሣዊ መሢህ በደብረ ዘይት

፩· በማቴዎስ ወንጌል በ፳፬ኛው ፣
ሲነገር ይኖራል የክርስቶስ መምጫው ።
፪· እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ ፣
የቁርጥ መምጫውን ቃሉን ጠቀለለ ፣
(እንዳያስቷችሁ ተጠንቀቁ እያለ ፤)



፫· ፴ኛ ቁጥር በዚሁ ምዕራፍ ፣
የጦርነትን ቃል ያሳያል በሰልፍ ።
፬· ይህ ሁሉ ምሳሌ ለማን ይመስልሃል ፣ ?
የዓለም ፍጻሜ መሆኑን አስተውል ።
፭· አንተ ግብዝ ሥጋ በከንቱ እንዳትቀር ፣
ማወቅ ይገባሃል ይህን ሁሉ ነገር ።
፮· ምሳሌው ብዙ ነው የክርስቶስ መምጫ ፣
ከከብ, ተመልከቱ በስከ ፀሐይ መውጫ ።
፯· በክረምት እንዳይሆን የእኛ ስደታችን ፤
በ፳ኛው ቁጥር አዘዘ ጸሎትን ።
(እንግዲህ እንጸልይ ክዚህ እንድንድን)

ባልጠረጠራችሁበት ሰዓት የሰው ልጅ ይመጣልና ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ። ማቴ ፳፬ (፵፬ ።)

## መዝሙር ፱

## ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ርግመተ

## በለስ ።

፩· በማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ድ ፣
ሲመሩን ይታያል በረቂቅ መንገድ ።
፪· የኛ ሆሣዕና መድኃኒታችን ፤
ሊጐበኛት ሄደ ቤተ መቅደስን ።

www.ethiopianorthodox.org

፫. በተባረከችው በዳዊት መንግሥት ፣
መጣ ሆሣዕና የእኛ መድኃኒት ።

፬. ሆሣዕና ማለት መድኃኒት መሆኑን ፣
እንግዲህ ሁላችን እንወቅ ይህንን ።

፭. የበለስ ልምላሜ ቢታየው ከሩቅ ፣
ወደ እርሷ ቀረበ ፍሬ ሊጠይቅ ።
( የማይራብ አምላክ የርኁባን ስንቅ ) ።

፮ ፍሬ ቢጠፋበት በዚያችም በለስ ፣
በጣም ረገማት ንጉሥ ክርስቶስ ፣
( እንጨቷ እስኪሰበር ሥሯም እስኪፈልስ ) ።

፯ እንግዲህ ሕፃናት እንወቅ በጣም ፣
ፍሬ ከእኛ ጠፍቶ እንዳንረገም ።

፰ መረገም ክፉ ነው ከዚህ ሁሉ ነገር ፣
መሠረትን ነቅሎ አጥንትን የሚሰብር ።

የሰው ልጅ ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ይሰጥ ዘንድ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም ። (ማቴ ፳፥ ፳፰ ።)

## መዝሙር ፲ ፤

## ስቅለተ ክርስቶስ ።

፩ ሉቃስ ወንጌላዊ ምዕራፍ ፳፫ት ፣
ጉልቶ ይታየናል የአምላክ ስቅለት ።



አምላክ ለእኛ ብሎ ቢያፈሰው ደሙን ፣
ለምን ከለከለች ፀሐይ ብርሃኗን ።

፫ አንቺ ዕለተ ዓርብ ከሁሉ በለጥሺ ፣
ለማያልቀው ሥጋ ገበያ ሁነሺ ።

፬ ከማያልቀው ሥጋ ሰዎቹ ቢበሉ
ገነት ገብተው ቀሩ ሳይከለከሉ ።

፭ ይህንንም ሰምቶ ሲኦል የወረደ ፣
የበላ አመለጠኝ ብሎ ተናደደ ።

፮ የከበረ ሥጋ የከበረ ደም ፣
በመስቀል ላይ ዋለ ኢየሩሳሌም ።

፯ በሥጋችን ሐኪም ዓለም ተታለለ ፣
ነፍስን የሚያድናት ደጉ ሐኪም ሳለ ።

፰ ይኸ ደጉ ሐኪም የማይፈልግ ዋጋ ፣
ነፍስንም ሥጋንም ያድናል ካደጋ ።

፱ መዳን የምትፈልግ ላሳይህ ቤቱን ፣
በሰላም ጠይቃት ቤተ መቅደስን ።

በክብር ዋጋ ተገዝታችኋልና እንግዲያስ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡ (፩ ቆሮ ፮ ፳ ።)

## መዝሙር ፲፩ ።

## ብርሃነ ትንሣኤ ለክርስቶስ ።

፩ ዮሐንስ ወንጌል ፳ው ምዕራፍ ፣
ትንሣኤው ተሰማ ከማርያም አፍ ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ የመግደላዊት ሴት አንቺ ማርያም ፣
የትንሣኤውን ቃል አፅማሽ ላለም ።

፲ በጣም የበዛ ነው የማቴዎስ ሀብቱ ፣
( ምዕራፍ ፳፰ት ብትመለከቱ ) ፤
የትንሣኤው ብርሃን ያበራል ከፊቱ ።

፲፩ በሽተኛ ሆነች ይህች መቃብር ፣
የበላችው ሥጋ ከሆዷ አያድር ።

፲፪ የመቃብር ፍዳ ሥጋን የሠረቀ ፣
በገዛ እጁ ጕርሶ ጕሮሮው ታነቀ ።

፲፫ በሥጋ ገበያ ከመዋል እራቁ ፤
ብርታት ባለው መንፈስ እንድትጠበቁ ።

፲፬ የሥጋ ገበያ በሁለት ቢመረመር ፤
አንደኛው ለሕይወት አንደኛው ለኃሣር ።

፲፭ እውነተኛው ሥጋ የሚዋሀዳት ፣
የመንፈስ ማደሪያ ቤተ መቅደስ ናት ።

እርሱ ስለ ኃጢአታችን ቤዛ የተሰጠ ስለ ጽድቃችንም የተነሣ ።( ሮሜ ፬ ፡ ፳፭ )

## መዝሙር ፲፱ ።

## ዳግም ትንሣኤ ።

፩ በሞት ጥላ ላሉ ብርሃን ወጣላቸው ፣
የትንሣኤ ፀሐይ ቢቆም ከፊታቸው ።



፪ ይኸ የሞት ጥላ ሕዝቡን የሰወረ ፤
በትንሣኤ ብርሃን ኃይሉ ተሰበረ ።

፫ ሞት ገዳይ ነበረ እስከ ዛሬ ድረስ ፣
ዛሬስ ሞት ወደቀ እንዳይገድል በነፍስ ።

፬ የትንሣኤ ልጆች በጣም ተደሰቱ ፤
ለእኛም ዕድል አለን በዳግም ምጽዓቱ ።

፭ ሞት የሰው ክፉ ነው የሴለው ማዕርግ ፣
አንበሳ ሰበረው ሥጋ ሲፈልግ ።

፮ ሲሠርቅ የለመደ ከድሆቹ ቤት ፤
በብርሃን ተያዘ ይኸ ሌባ ሞት ፡

፯ የዘላለም ብርሃን መጥፋት የሌለበት ፤
የሞትን ጨለማ ድንዓቱን ሻረበት ።

፰ የትንሣኤ ፀሐይ በጣም የሚያስፈራ ፤
አሳርሮት ቀረ የሞትን አዝመራ ።

፱ ሞትን የሰበረ የነፃነት ጌታ ፤
ዘለዓለም ንዋሪ ነው ኃይሉ እንደበረታ ።

እርሱ ከዚህ የለም ነገር ግን ተነሣ፥ አሰቡ እንደነገራቸው እርሱ ገና በገሊላ ሳለ፥( ሉቃ ፳፬- ፭ ፮ ) ።

## መዝሙር ፳

## ዕርገተ ክርስቶስ

፩ በ፳፬ ምዕራፍ ቁጥር ፶፩ድ ፤
ሉቃስ ያሳዩናል የዕርገቱን መንገድ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

፪ ክብሩን አስረድቶ ለሐዋርያት ፣
ወዲያው ተመለሰ ወደ መጣበት ።
፫ ከድንግል ማርያም የተገኘው በኩር ፣
ሥጋን ከመለኮት የሚያስተባብር ።
፬ ሰማይና መሬት ምንም ቢራራቁ ፣
ዕርገት ወሰናቸው መሆኑን ዐወቁ ።
፭ ወደ ሰማይ ቢሄድ የከበረ ሥጋ ፣
እንግዲህ ሁላችን መምጣቱን እንዘንጋ ።
፮ አይመጣም አትበል አንተ የሰው ልጅ ፣
መመለስ ልማድ ነው የሄደ ወዳጅ ።
፯ ልጅ ማለት እንዲህ ነው የሌለው ድካም ፣
ካባቱ ተልኮ ሥራን መፈጸም ።
፰ ሥራውን ፈጽሞ ቢመለስ ካባቱ ፣
በቀኝ ተቀመጠ እንደ ልጅነቱ ።
፱ እኛንም በቀኙ እንዲያስቀምጠን ፣
የተናገረውን እንጠብቅ ሕጉን ።

እርሱ ሲባርካቸው ከርሳቸው ራቀ ወደሰማይም ወጣ።
( ሉቃ ፳፬ ፶፩ )

## መዝሙር ፲፬

## ጰራቅሊጦስ በጰንጠቆስጤ

፩ ግብረ ሐዋርያት ከ፪ቱ ምዕራፍ ፣
ስለ ጰራቅሊጦስ ምንም አንስነፍ ፣
( ሲያናግር ይሰማል በማናውቀው አፍ ) ።



፪ የጰራቅሊጦስ ኃይል በጣም የረቀቀ ፣
በጰንጠቆስጤ ነው ክብሩ የታወቀ ።
፫ ጰራቅሊጦስ ማለት መንፈስ ቅዱስ ነው ፣
ሁሉን እንደሥራው የሚያናግረው ።
፬ ዕውቀት ለሌላቸው ለሐዋርያት፣
የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሆናቸው ዕውቀት ፣
( ቋንቋ እስኪናገሩ በ፸፪ት ) ።
፭ ደግሞ በዚህ ብቻ እንዳይወሰን ፣
በሐዋርያት ቃል ላኩ ሃይማኖን ።
፮ ቀናዒ መሆን ነው ለፈጠረን ጌታ ፣
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንድንበረታ ።
፯ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሰጠው ብርታት ፣
ዘለዓለም ይኖራል ገብቶ ከገነት ።
፰ አንቺ የገነት በር የማያውቅሽ ቀሬ ፣
ቅልፍሽ መንፈስ ቅዱስ ተከፈተ ዛሬ ።

ያንን አባቴ በስሜ የሚሰደውን የሚያጽናና መንፈስ ቅዱስ እርሱ ሁሉን ሊያስተምራችሁና የነገርኋችሁን የሆነውን ሁሉ ሊያሳስባችሁ ነው ( ዮሐ ፲፬፡ ፳፮

## መዝሙር ፲፭

## ብርሃነ መለኮት በደብረ ታቦር

፩ ምዕራፍ ፲፯ በማቴዎስ ቃል ፣
ለነቢያት ታየ የክርስቶስ ኃይል ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ የታቦር ተራራ በጣም የረዘመ ፣
የመለኮት ብርሃን ኃይሉ በርሱ ቆመ ።

፫ መሰወሩን ሳያውቅ በብሩህ ደመና ፣
ቤት እንሥራ ይላል የጴጥሮስ ሕሊና ።

፬ እጅግ ያስደንቃል የክርስቶስ ሥራ ፣
ልጅነቱን ሰማን ከረጅም ተራራ ።

፭ ከረጅም ተራራ በቆመው ሐውልት ፣
ተቀርጾ ይታያል ያምላክ ልጅነት ። ፣

፮ ሙሴ ሞት ተመኘ በደብረ ታቦር ፣
ተገልጦ ቢታየው የመለኮት ክብር ።

፯ እንዲህ ያስፈራን የርኅራኄ ክብርህ ፣
በፍርድህስ ጊዜ ማን ይቆም ከፊትህ ፣ ?
( እንደኛም አይደለ እንደ አምላክነትህ ) ።

፰ በደብረ ታቦር ላይ የመጣው ብርሃን ፣
የገነትን መንገድ ቅጽፈን አሳየን ።

፱ የመለኮት ብርሃን የማይመረመር ፣
በታቦር ላይ ታዩ ተገልጦ ለፍጡር ።

፲ አምላክ ያፈቅረዋል የሰውን እምነት ፣
መለኮቱን ገልጾ እስከ ማሳየት ።

እሱ የማይታይ የእግዚአብሔር ምሳሌ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው ። (ቆላ ፩ ፣ ፲፭)



## መዝሙር ፲፮

## ማኅበራዊ ጸሎት ዘዘወትር ።

ለዘለዓለሙ በስም በአካል ሦት ፤ በባህርይ በህልውና አንድ አምላክ በሚሆኑ፣ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም፣ በአንዲት ቃል ዓለምን ሁሉ በፈጠረ ፣ ክቡር ምስጉን በሚሆን፣ ጌትነቱ በሰማይ በምድር ምሉዕ፣ አሸናፊ የሠራዊት ጌታ፣ ኃያል፣ ጽኑዕ፣ ንጹሕ፣ ክቡር ፣ በሚሆን፣ ቅድመ ዓለም በነበረ፣ ዓለምን አሳልፎ በሚኖር፤ በርሱ ስም አምነን ፣ ለአብ ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ፣ እንሰግዳለን አሜን ።

ቀ ፩ ለዘለዓለሙ በስም በአካል ሦት ፣
ብለን እንጠንቅቅ የሥላሴን ምልአት ።

፪ በባሕርይና በሕልውና ግን ፣
ሦትነቱን እወቅ አንድ አምላክ መሆኑን ።

፫ በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ፣
ሦትነት ካንድነት እንዳለ እናስታውስ ።

፬ ደግሞም ላሸናፊ ለሠራዊት ጌታ ፣
ለረቂቅ ነገሩ የለውም ሐተታ ። ( ምርምር )

፭ የሠራዊት ጌታ በጣም የከበረ ፣
ዓለማትን ሁሉ ባንዲት ቃል ፈጠረ ።

፮ ለዘለዓለም እሱ መሆኑን አውቀን ፣
ጉድለት እንዳይኖረው ለአምልኮታችን ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org


፯ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ፣
መስገድ ይገባናል በሥጋም በነፍስ ።
፰ ጣዖትን በማምለክ ሕዝቡ ሲዋረዱ ፣
በአብና በወልድ በመንፈስ ታገዱ ።
፱ እሑን ትባረክ ዘንድ ማኅበራችን ፣
ፈጥነህ ላክልን ጰራቅሊጦስን ።

ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል ፣ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል ። ( ሉ ቃ ፲፬፡ ፲፩ )

## የጸሎት መዝሙር ፲፯

፩ ከመቶ ፴ መዝሙረ ዳዊት ፣
አምላክን እንለምን የኛን መድኀኒት ።
፪ ወዳንተ እንጮኻለን አቤቱ ጌታችን ፣
ከፊትህ እንዲደርስ በጣም ጩኸታችን ቁ፡፩
፫ ብትጠባበቃት አቤቱ ኃጢአትን ፣ ቁ ፪
ማን ይቆም ከፊትህ አንተ ስትጠራን ።
፬ ሰዎች ይፈሩህ ዘንድ ይቅርታ ካንተ ነው ፣ ቁ
እንደ ቸርነትህ ዓለሙን አድነው ።
፭ እግዚአብሔርን ተስፋ ያደረግን ስንሆን ፣ ቁ ፭
አይጠረጠርም እንድትድን ነፍሳችን ።
፮ ፮ተኛ ቁጥር በዚሁ መዝሙር፣ ቁ ፮
እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን በምር ።

ሃያ ስባት መዝሙር ።






www.ethiopianorthodox.org

፯ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋ ብዙም መድኀኒት ፣
እንዲገኝ ተጽፏል በብዙ ጸሎት ።
፰ አሥረኛ ምዕረፍ በዳንኤል ውስጥ ፣
ከቶ የጾም ሕግ ተጽፏል በርግጥ ። ቁ ፬
፱ እኛም በጾማችን እንደ ዳንኤል ፣
ሥጋም አንበላ ማልፈያም መብል ።
፲ በ፫ኛው ቁጥር በዚሁ ምዕራፍ ፣
ወይንም አልቀመሰ የዳንኤል አፍ ። ቁ ፫

## የጸሎት መዝሙር ፲፰

፩ ፳፮ት መዝሙር ዳዊት የሚለው
እግዚአብሔር ብርሃኔ ረድኤቴ ነው ።
፪ እግዚአብሔር ብርሃኔ ረድኤቴ ሲሆን ቁ ፳
ምን ይነካኛ ብዬ እኔ ልፍራ ከማን ። ቁ ፩
፫ ከኔ ቀርበው ነበር አስጨናቆች ሁሉ ፪
ሰብብር ጣላቸው ያምላክነት ኃይሉ ።
፬ በ፫ኛው ቁጥር በዚሁ መዝሙር ፣ ቁ ፫
ምንም ልቤ አይፈራ ሠራዊት ቢሰፍር ።
፭ የሚለው ቃል ለኛ የተጻፈ ሲሆን ፣
ምንም ከእኛ አይለይ ሕያው አምላካችን ።
፮ አቤቱ አባታችን ቃላችንን ስማ ፣ ቁ ፲
ተሰውረን ቀረን በኃጢአት ጨለማ ።
፯ ለኃጢአት ጨለማ ብርሃን አንተ ነህ ፣
አቤቱ አስበነ እንዳንቀር ሕዝብህ ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ አቤቱ አንዲት ነገር ካንተ እንለምናለን ፣ ቁ ፬
ከቤትህ አድርጋት የሕይወትን ዘመን ።

### የጸሎት መዝሙር ፲፱
### ከዳዊት መዝሙር ፶፬ የተጠቀሰ

፩ አቤቱ በስምህ አድነኝ ጌታዬ ፣ ቁ ፩
በጉልበትህም ፍረድ እንዳትወድቅ ሥጋዬ ።
፪ አቤቱ ጌታዬ ጸሎቴንም ስማ ፤ ቁ ፪
እንደ መላእክትህ እንዳሉት በራማ ።
፫ ኃያላንም ቆመው እኔን ይሹታል ፣
አቤቱ አምላኪየ አድነኝ ከሁሉ ።
፬ ዓይኔ በጠላቴ ደስታዋን አየች ፣ ቁ ፯
አምላክ ተመልከቶ እንደ ተበደለች ።

### የጸሎት መዝሙር ፳
### ከዳዊት መዝሙር ፶፩

፩ እንደ ቸርነትህ አቤቱ ማረኝ ፣ ቁ ፩
እንደ ምሕረትህም ይቅርታ ስጠኝ ።
፪ ከኃጢአቴም አንፃኝ ከብዙም በደሌ ፣
ለዚያች ከፉ ኃጢአት እንዳልሆናት ሎሌ ። ቁ ፪
አዝ አሁን ትባረክ ዘንድ ማኅበራችን ፣
ፈጥነህ ላክልን ጰራቅሊጦስን ።

## እንደ ፡ ቸርነትህ ።






www.ethiopianorthodox.org

፫ እኔም አመፃዬን በደሌን ሳውቀው ፡
ከቶ የሚያድነኝ ቸርነትህ ነው ። ቁ ፫
፬ አንተን ብቻ በደልሁ ክፉ ም አደረግሁ ፡
አሁን ይቅር በለኝ ከፊትህ ወደቅሁ ። ቁ ፬
አዝ. አሁን ትባረክ ዘንድ ማኅበራችን
ፈጥነህ ላክልን ጰራቅሊጦስን ፡
፭ ከፊትህ ወድቄ ስለምን አንተን ፡
መውደቄን ተመልከት አምላከ ብርሃን ፡
አሁን ትባረክ ዘንድ ማኅበራችን ።
ፈጥነህ ላክልን ጰራቅሊጦስን ።

ክፍል ፡

፩ እናቴ በኃጢአት እንዳረገዘችኝ ፡ ቁ ፭
የሥጋ ልደቴ አመፃ ሆነችኝ ።
፪ ከበረዶም አንፃኝ አቤቱ ጌታዬ ፡ ቁ ፯
በሂሶጵም እርጨኝ እንደ ለመናዬ ።
፫ ሐሤት ደስታህን አሰማኝ አቤቱ ፡ ቁ ፰
ሰባራ የሆኑት አጥንቶችም ይርቱ ።
፬ ከኃጢአቴ ሰውር ጌታ ሆይ ፊትህን ፡ ቁ ፱
በደሌንም ሁሉ ደምስስ በሥልጣን ።
፭ አቤቱ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ አንተ ፡ ቁ ፲
መንፈሴም እንዳይቀር ፈጽሞ እንደ ሞቀ ።

www.ethiopianorthodox.org

## መዝሙር ፷፩ ፣

### ከዳዊት መዝሙር ፶፩ ፣

ቁ ፩ አቤቱ አባት ሆይ ይቅርታ ስጠኝ ፣ ቁ ፲፩
ቅዱስ መንፈስህንም አትውሰድብኝ ።
፪ ለተላላፊዎችም ሕግህን ነገርሁ ፣ ቁ ፲፫
ኃጢአተኞችንም ወዳንተ መለስሁ ።
ቁ ፫ የመድኀኒቴ አምላክ ከደም አድነኝ ቁ ፲፬
ምላሴም ጽድቅህን ትሁን አመስጋኝ ።
፬ ከንፈሮቼን ክፈት አፌም ይናገር ቁ ፲፭
ምስጋናህ ብዙ ነው በሰማይ በምድር ።
፭የእግዚአብሔር መሥዋዕት የቀና መንፈስ ነው ቁ ፲፯
ይህን መጥፎ መንፈስ አቤቱ አንተ አድነው ።

## መዝሙር ፷፪

ቁ ፩ መዝሙር ፻፪ ያዘነ መንፈስ
ልመናውን ለአምላክ ይታያል ሲያፈስ ።
፪ አቤቱ ጌታዬ ጸሎቴን ስማኝ
ጩኸቴም ወዳንተ እንዲደርስልኝ ። ቁ ፩
፫ በመከራዬ ቀን ፊትህን ከኔ አትሰውር
በጠራሁህም ቀን አትዋል አትደር ። ቁ ፪
፬ አጥንቴ እንደ ቆሎ ተቆረጠመች
ዘመኔም እንደ ጢስ ፈጥና አለፈች ። ቁ ፫



፭ ልቤ ጠቁሮ ቀረ እንደ ጠለሸት
እጅግም እረሳሁ እንጀራ መብላት ቁ ፬
፮ ከለቅሶዬ ብዛት በጣም የተነሣ
የሰውነቴ አጥንት ሥጋዬን እረሣ ። ቁ ፭
፯ የውድማውን እርኩም እጅግም መሰልሁ ፯
ከባድማም ቦታ እንደ ጉጉት ሆንሁ ።
፰ በኔም ላይ ጠላቶች አላገጡብኝ ቁ ፰
ያሚያሳድዱኝም ተማማሉብኝ ቁ ፱
፱ መጠጤን ከንባ ጋር እየቀላቀልሁ
አመድ እንደ እንጀራ ሁልጊዜ በላሁ ።
፲ ዘመኔ እንደ ጥላ ፈጥኖ አለፈብኝ ቁ ፲
እንደ አምላክነትህ አቤቱ ማረኝ ።

## መዝሙር ፷፫

### ከዳዊት መዝሙር ፻፪

፩ አንተ ትነሣለህ ጽዮንን ልትምር ፣ ቁ ፲፫
የምሕረቷ ጊዜ ነውና በምር ።
፪ አሕዛብም ሁሉ ስምህን ይፈራሉ ፣ ቁ ፲፭
ነገሥታትም ደግሞ ይንቀጠቀጣሉ ።
፫ ከችግረኞች ዘንድ ዓይቶ ጸሎትን ፣
እግዚአብሔር አልናቀም ልመናቸውን ፣ ቁ ፲፯
፬ ይህ ለምትመጣው ትውልድ ይጻፍልን ፣ ፲፰
የሚፈጠረውም አምላኩን ያመስግን ።

www.ethiopianorthodox.org


፭ የታሠሩትንም ልቅሶ ይሰማ ዘንድ ፣
አቤቱ እንበለው ሁላችን አንድ ባንድ ። ቁ ፳
፮ ወዳንተ ሲያለቅሱ ለሞት ተመድበው ፣
አቤቱ ይቅር በል ይቅርታ ካንተ ነው ።
፯ ሕዝቦች እንዲያበቡ በጽዮን ያንተን ስም ፣ ፳፩
ምስጋናቸውንም በኢየሩሳሌም ።
፰ ለልጅ ልጅ ሲሆኑ እሊህ ዓመታቱ ፣
በኩሌታ ዘመን አታንግሣኝ አቤቱ ። ፳፬
፱ ከጥንት ጀምረህ ምድርን መሠረትኸው ፣ ቁ ፳፭
ሰማዮችም ሁሉ የእጅህ ሥራ ናቸው ፣
፲ እሊህ ሁሉ እንደ ልብስ ሲያልቁ አርጂተው ፣
ለዘለዓለሙ አንተ ነህ ሕያው ። ቁ ፳፯
፲፩ አባት ለልጆቹ ፈጥኖ እንደሚራራ ፣
አምላክም ይራራል እርሱን ለሚፈሩ ። ቁ ፲፫

## መ ዝ ሙ ር ፻፪

### ዳዊት መዝሙር ፻፫

ቁ ፩ እግዚአብሔርን ባርኪ ነፍሴ ዘለዓለም ፣ ቁ ፩
የተቀደሰውን ስሙን አጥንቴም ።
፪ ላንች የሆነውን በጎውን አትርሺ ፣ ቁ ፪
ደዌሽንም ሁሉ ስለፈወሰሽ ።
አዝ / ሁሉም ዓለማት ሁሉም ዓለማት ፣
ባንተ ቃል አገኙ ድኅነት ።

## እግዚአብሔርን ባርኪ ።






www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

፫ እግዚአብሔር ያደርጋል ለተበደሉት ፣ ቁ፯
ጽድቅንና ፍርድን በብዙ ጸሎት

፬ እግዚአብሔር መሐሪ ጸጋ ሰጭ ነው ፣ ቁ ፰
ቁጣው የዘገየ ቸርነት ያለው ።
አዝ | ሁሉም ዓለማት ሁሉም ዓለማት ፣
ባንተ ቃል አገኙ ድኅነት ።

፭ ዘወትር አይወቅስም አምላከ ሰላም ፣ ቁ ፱
ፈጥኖም በሕዝቡ ላይ አይቀየምም ።
አዝ | ሁሉም ዓለማት ሁሉም ዓለማት ፣
ባንተ ቃል አገኙ ድኅነት ።

## መዝሙር ፳፭

## የዓለም ከንቱነት ።

፩ በዓለም ጥላ ማረፍ አይምሰለን ጤና
ዓለም ከንቱ ጥላ ትሂዳለችና ።
፪ ዓለም ጥላ ስትሄድ ፀሐይ ሲበረታ
ደከሞ ወድቆ ቀረ የሰው ልጅ አውቃታ ።
፫ ላፈርሰው ነው ብለህ አትዘጋ ቤትህን
ዘላለም የማይፈርስ ቤት እያለልን ።
፬ ዓለም ማረፊያ ናት መኖሪያ ገነት
ተነሡ እንከተል እኛም ከሄዱት

፰ አፈር ከሸተተን ከያዘን በሽታ
ቁንቆርብ አንድንም ይህን ጊዜ እንበርታ ።
፱ መቁረብ በሕይወት ነው ንስሐ መግባት
ይህ ሁሉ አይገኝም ከገቡ መሬት ።
፲ ሰዎች ተጠንቀቁ እወቁ ሁላችሁ
ዓለም አታላይ ናት እንዳትሠርቃችሁ ።

## አዝማች ።

ከዚህ ፀታች ያሉት አዝማቾች በማንኛውም የመዝሙር ድምፅ ሊገቡና ሊዘመሩ ይችላሉ ።

፩ኛ አሁን ትባረክ ዘንድ ማኅበራችን
ፈጥነህ ላክልነ ጰራቅሊጦስን ።

፪ኛ ሁሉም ዓለማት ሁሉም ዓለማት
ባንተ ቃል አገኙ ድኅነት ።

፫ኛ በርግብ አምሳል ወረደ በርግብ አምሳል
ወረደ መንፈስ ቅዱስ
በርግብ አምሳል ወረደ በርግብ አምሳል
ወረደ ጰራቅሊጦስ ።

## መዝሙር ፷፮

፩ አቤቱ አምላኪዬ እማልድሃለሁ
ነፍሴ እንደተጠማች ወዳንተም እያለሁ ፣ መዝ ፷፫ ቁ ፩



፪ ኃይልህን በመቅደስ አሁን ስላየሁ
ክብርህን ለመግለጽ እናፍቃለሁ ። ቁ ፪
ትሻላለችና ምሕረትህ ከሕይወት
ፈጥነው ያመሰግኑ ከንፈሮቼም በውነት ። ቁ ፫
፬ እንዲህ በሕይወቴ እያመሰገንሁ
በስምህ እጆቼን አሁን እነሣሁ ። ቁ ፬
፭ በመኝታዬና በትጋቴ ሳስብ
የሀሳብ ፈጻሚ መንፈስህ እንዲቀርብ ። ቁ ፮
፮ ረድኤቴ አንተ ነህ ለሕይወቴም ጤና
በክንፎችህ ጥላ ደስ ይለኛልና ። ቁ ፯
፯ ነፍሴ በአንተ ኋላ ፈጽማ ተጣብቃ
ቀኝህም ደገፋ ሆነኝልት ጠበቃ ። ቁ ፰
፰ ነፍሴንም ሊያጠፉ ሁልጊዜ የሚሹዋት
በረቂቁ ፍርድህ ይገባሉ መሬት ። ቁ ፱
፱ የቀበሮ ፈንታ ሆና ሕይወታቸው
በሰይፍ እጅ ወደቁ ቀረ ምኞታቸው ። ቁ ፲
፲ በአንተ የሚምሉ እልል አሉ በጣም
አፉቸው ተዘጋ የሐሰተኞችም ። ቁ ፲፩

## መዝሙር ፷፯

፩ አቤቱ በጽዮን ለአንተ በዝምታ መዝ ፷፭ ቁ ፩
ማመስገን ይገባል ጥዋትና ማታ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ አንተ ጸሎት ሰሚ ስለሆንህልን ቁ ፪
ሥጋ ሁሉ መጣ ወዳንተ እንዲድን ።
፫ መተላለፋችን ቢበረታብን ቁ ፫
ፈጥነህ ይቅር አልኸን አመፃችንን ።
፬ አንተ የመረጥኸው ምስጉን ነው በረትህ ቁ ፬
በረከት ጠግበን ከቤተ መቅደስህ ።
፭ የመድኃኒታችን አምላክ አንተ ሳለህ ቁ ፭
የሚያስፈራንንም ትመልስዋለህ ።
፮ ተራሮቹ ጸኑ አምላክ በጉልበቱ ቁ ፮
እንዲሁም ለሥጋ እሱ ነው ሕይወቱ ።
፯ ዝም እንዳሰኘልን የበሕሩን ድንፋታ ቁ ፯
ያሕዛብን ሁከት ዝም ያሰኛል ጌታ ።
፰ በምድር ዳርቻ የሚኖሩ ሁሉ ቁ ፰
አምላክ ታምራትህን በጣም ይፈራሉ ።
፱ ምድርን ጐበኘሀት በጣም ረካች ቁ ፱
ባለጸግነትም እጅግ አበዛች ።
፲ የሁሉንም ሃሳብ አንተ ታውቀዋለህ
ምሕረትህን ሙላበት ጥፋትን አውጥተህ ።

## መዝሙር ፳፰

፩ ቃሌን አድምጥልኝ አሳቤን አስተውል መ ፭ ቍ ፩
ምሕረትህንም አዝንም ፣ በሕዝብህ እንደ ጠል ።



፪ ንጉሤም አንተነህ አምላኪየም አንተ ቍ ፪
ጩኸቴን ስማልኝ ስጸልይ ወዳንተ ።
፫ አቤቱ ስትሰማ ድምጼን በማለዳ ቍ ፫
አንተ ደምስስልኝ ያለብኝን ፍዳ ።
፬ ክፋን የምትወድ አይደለህምና ቍ ፬
ባንተ ዘንድ አያድርም ያልቀና ህሊና ።
፭ ካይንህ ፊት አይቆሙም በከንቱ እሚመኩ ቁ ፭
አትፈልግምና ሁሉን እንዲነኩ ።
፮ ሐሰት ቢናገሩ ፈጥነህ ታጠፋለህ ቁ ፮
ሸንጋዩንም ደግሞ ታጥርደዋለህ ።
፯ በምሕረትህ ብዛት ወዳንተ እገባለሁ ቁ ፯
በቅድስናህም መቅደስ እሰግዳለሁ ።
፰ አቤቱ በጽድቅህ አንተ እንድትመራኝ ቁ ፰
ስለ ጠላቶችም መንገድህን አቅናልኝ ።
፱ በአፋቸው አልገባም ፈጽሞ ቅንነት ቁ ፱
ልባቸውም ይሻል ፍጥረትን ለማጥፋት ።
፲ ክፉ ጉሮሯቸው እንደ መቃብር ቍ ፲
በጣም ተከፍታለች ሰውን ልትሰውር ።

## መዝሙር ፳፱

፩ ሕጉን የሚያነቡ ቀንና ሌሊት መዝ ፩ ቁ ፪
ከእግዚአብሔር አገኙ ክብርና ሕይወት ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ደግሞም እንዳንዲት ተክል በውሀ እንደበቀለች ቁ ፫
ልምላሜና ፍሬን ክብራቸው አሳየች ።

፫ እንደምን ይገርማል ስምህ ጌታችን መዝ ፰ ቁ ፩
ሰማይና መሬት አልቻሉም ኃይሉን ።

፬ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ቁ ፪
ኃይልን አዘጋጀህ ጠላትህ እንዲያርፍ ።

፭ ሰማዮችንና ከዋክብትን ሁሉ ቁ ፫
አንተ ሠራሀቸው እንዲያገለግሉ ።

## መዝሙር ፴

<u>የሐና ጸሎት</u> መጽሐፈ ሳሙኤል ቀ|ም ፪

፩ ልቤ በእግዚአብሔር ሐሤት ያደርጋል ቁ ፩
ክብሬም በአምላኬ ከፍ ከፍ ይላል ።

፪ ከፋችሁ አይውጣ የኩራት ነገር ቁ ፫
የትዕቢትም ነገር ከናንተ ይሻር ።

፫ የውቀት አምላክ እሱ እግዚአብሔር ሲሆን » »
ሥራ ሁሉ በርሱ ተመዘነ አሁን ።

፬ ጠግበው የነበሩ ለእንጀራ ተገዙ ቁ ፭
የተራቡም ደግሞ አገኙ በብዙ ።

፭ ብዙ የምትወልድ ፈጥና ስትደክም » »
መካኒቱ ሰባት ወለደች ባንተ ስም



፮ እግዚአብሔር ያድናል ይገድላልም ፈጥና ቁ ፮
ከሲኦል ያወጣል እንዲሁም ኰንኖ።

<u>ክፍል</u>

፯ ደሀ ከደረገን ከዋረደን ወዲያ ቁ ፯ መጽ ሳሙ ቀም፪
ከፍ ከፍ አድርጎ ያነሣናል ከዚያ

፰ ችጋረኛውንም ከመሬት ያነሣል ቁ ፰
ምስኪኑንም ደግሞ ከትድፍ ያወጣል ።

፱ ካለቆቹ ጋራ ሊያስቀምጠው እሱን » »
ፈጥኖ አዘጋጀለት ሞገስና ክብርን ።

፲ የምድር መሠረት ለእግዚአብሔር ናትና
እንግዲህ ሁላችን እሱን ደጅ እንጥና ።

፲፩ ብርቱ በብርታቱ ስለማይጠነክር ቁ ፱
እርሱ ይጠብቃል የጻድቃኑን እግር ።

፲፪ ካንተ ጋር ቢጣሉ ፈጥነው ይደቃሉ ቁ ፲
በሰማይ ነጐድጓድ በሚያስገርም ቃሉ ።

፲፫ እግዚአብሔር ይሰጣል ለንጉሡ ኃይል » »
የመሲሁንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል ።

## መዝሙር ፴፩

፩ ሃሌ ሃሌ ሉያ እግእዚብሔር ፈጣሬ
ቸርነትህ መልካም ዘለዓለም ነዋሪ መዝ ፻፮ ቁ ፩

www.ethiopianorthodox.org

፪ ማነው የሚናገር የእግዚአብሔርን ኃይል
ደግሞስ ምስጋናውን ለማን ያሰማል ቁ፪

፫ ፍርድ የሚጠብቁ ይመስገናሉ ቁ ፫
እንዲሁም ለጽድቅህ ፈጥነው የሚያደሉ

፬ አቤቱ ለሕዝብህ በሰጠኸው ተስፋ ቁ ፬
መድኃኒት ይሁነን የጸጋህ ደገፋ

፭ አቤቱ ለሕግህ መንገድ አስተምረን መዝ ፻፲፰ ቁ
እስከ መጨረሻም አንተው እንድትመራን

፮ በፊቴ ላይ አብራው የፍቅርህን ፋና
ፈጥኜ እንድይዘው በፍጹም ሕሊና

፯ በትእዛዝህ መንገድ አመላልሰኝ ጌታ
አንተን እንዳስብህ ጠዋትና ማታ

፰ ለሚፈራ በርያህ ትእዛዝህን አጽናለት
ርኅሩኅ ነህና አምላካችን በውነት

፱ እነሆ ትእዛዝህን ናፈቅሁ አምላኪየ
የጽድቅህም ሕይወት ይቁም ከኋላየ

## መዝሙር ፴፪

፩ የእግዚአብሔርን ስሙን አመስግኑ መዝ ፡ ፻
በሉ ሃሌ ሉያ ክብሩንም አጋኑ ።

፪ የምትቆሙ ሁሉ በአምላካችን ቤት ፣ ቍ ፪
ወደሱ ተጓዙ እሱ ነው ሕይወት ።

፫ ጌታን እንለምን እሱ ቸር ነውና ቍ ፫
ለስሙም ዝማሬ እናቅርብ ምስጋና ።



፬ አምላክ ያሳየናል ከምድር ዳር ጉምን ቁ ፯
እንዲሁም ያደርጋል ለዝናም መብረቅን ።

፭ ለአምላኮች አምላክ አቅርቡ ትሕትና ።
እሱ ቸርነቱ ዘላለም ነውና ።

## መዝሙር ፴፫ ፡

፩ እግዚአብሔር ነገሠ ምድር ሐሤት ታድርግ መዝ ፺፮
ብዙ ደሴቶችም ደስ አላቸው እጅግ

፪ ደመናና ጭጋግ እጅግ በዙሪያው ነው ቁ ፪
እውነትና ፍርድም በዙፋኑ ደጅ ነው ።

፫ የእሳት ነበልባል በፊቱ ይነዳል ቁ ፫
ደግሞም ጠላቶቹን በዙሪያው ይፈጃል ።

፬ መብረቆቹም ሁሉ ለዓለም ነበሩ ቁ ፬
ምድርም ተናወጠች በሚያስገርም ክብሩ ።

፭ ተራሮች ቀለጡ እንደሰም በምድር ቁ ፭
በፍጥረቱ ጌታ በእግዚአብሔር

፮ እግዚአብሔር ልዑል ነህ በምድር ሁሉ ላይ ቁ፱
እጅግም ከአምላኮች የምትኖር በሰማይ ።

፯ ጻድቃን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ቁ ፲፩ ፲፪
ብርሃኑን ለናንተ ስለሰጣችሁ ።

## መዝሙር ፴፬

፩ ከኔ እንድታርቀው አምላክ እግዚአብሔር ምሳ፴ቁ፰
ከንቱ የሆነውን አሰተኛን ነገር ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ አምላክ እንዳትሰጠኝ የምለምንህን
ድህነትንና ባለጠግነትን ።
፫ ብቻ የሚያሻኝን እንጀራ ሥራልኝ ቁ ፱
ከጥጋቤ ብዛት ክጂህ እንዳልገኝ ።
፬ ደህም አታድርገኝ አምላኪየ አባክህ
በሐሰት ሰርቄ እንዳልምል በስምህ ።
፭ ከትዛዞች አንዱ አትስረቅ ለሚለው
በሕዝብ እንዲከበር እንዲሰማ አድርገው ።
፮ አምላክ ካንተ በቀር ሌላ ቸር የለም
ምሕረትህ ይጎብኘው እንዲድን ዓለም ።

መዝሙር ፴፭

፩ አቤቱ እስከመቼ ትረሳኛለህ መዝ ፲፫
እስከመቸስ ፊትህን ትሰውራለህ ።
፪ አቤቱ አምላኪየ የዓለም ረኛ
ዓይኖቼን አብራልኝ ለሞት እንዳልተኛ ቁ ፤
፫ እኔስ ታምኛለሁ በቸርነትህ ቁ፭
ልቤም ደስ ይለኛል በመድኃኒትህ ።
፬ አቀኝልታለሁ በረቂቅ ምሥጢር ቁ፯
ደኅንነት ለሰጠኝ ለእግዚአብሔር ።
፭ አቤቱ አምላኪየ ስማልኝ ጸሎቴን መዝ ፲፯
በቀና ህሊና የማቀርብልህን ።
፯ ልቤንም ፈተንኸው በሌሊት ጉብኝተህ ቁ ፫
አነጠርኸው በጣም ምንም አላገኘህ ።



፰ አፌ እንዳይሳደብ ፈቃዴ ነውና
ካጥፊዎቹም መንገድ ጠብቀኝ በጤና ።

መዝሙር ፴፮ ፣

፩ እንደ ዓይን ብሌኔ አምላክ ጠብቀኝ መዝ ፲፯ ቁ፰
በክንፍህም ጥላ ፈጥነህ ሰውረኝ ።
፪ ደሀ ባለጸጋ የማይል ፍርድህ
አምላክ ይድረሰኝ ደግሞም ምሕረትህ ።
፫ ዓለም በጊዜዋ ስታሰቃየን
እሷን እንድንንቅ ልቡና ስጠን ።
፬ ይህን ዓለም ንቆ ለጽድቅ የተራበ
ዘላለም ይኖራል እሱ እንደጠገበ (ጽድቅን ያገኛል) ።
፭ ትካዜያችን በዝቶ በጣም ከብዶብን
ወደንተ ቀርበናል አምላክ ደግፈን ።

መዝሙር ፴፯ ፣

፩ ሃሌ ሃሌ ሉያ እሱን አመስግኑት
ከወደቅን ወዲያ ላነሣን ከመሬት ።
፪ በጉልበቱም ጽናት እሱን አመስግኑት
ከወደቅን ወዲያ አውጥቶናል ከሳት ።
፫ አምላክን ማመስገን ደግሞም መለመን
በጥዋት በማታ ምግባችን ይሁን

www.ethiopianorthodox.org

፬ ወዳንተ ይጮሃል ፈራሽ በስባሽ ሥጋ
መንፈስህ ይጐብኘው እንዲድን ካደጋ ።

፭ ለጊዜው ስጠን አምላካችን ጤና
የሰው መጨረሻው መቃብር ነውና ።

፮ እሩን ከፍቶ ሊያየን ትልቁ መቃብር
ቆመን መሔዳችን ዕጹብ ነው ታምር ።

፯ አምላክ ልባችንን በመንፈስ ጐብኘው
ዓለምን እንዲንቅ ፈጥና እንዲተወው

መዝሙር ፴፰ ፡

፩ የኤልያስ አምላክ የቴስብያዊው
ስምህን ለሚጠራ ሕይወትን ስጠው ።

፪ ፈጽሞ ቢታመን ኤልያስ በስምህ
የሞት እጀናፊ ጐበኘው ሕይወትህ ።

፫ ሰማይና ምድርን ኤልያስ የዘጋ
አንተ ብትረዳው ነው ብትሰጠው ጸጋ ።

፬ የኤልያስ አምላክ የኤልያስ ጌታ
ሰረገላህ ይምጣ ሳለን በዚህ በታ ።

፭ አቤቱ ሥጋችን እጅግ በጣም ፈራ
ጥላውን ጥሎብን ያለም ሞት መራራ ።

፮ ሰው አይደለንም ወይ እኛስ ኢየሱስ
ምነው ከኛ ራቀ የሕይወት መንፈስ ።



፯ ከኢያሴንዩ ክቶና ተገኝቶ
ረገ ተዓ፡ ይህን ዓለም ትቶ ( ኤልያስ )

፰ ኤልያስ እንደኛ ሰው መሆኑን አውቀን
ርትተን እንጸልይ ከሞት እንድንድን ።

መዝሙር ፴፱ ።

ስለ ነገሥታት ጸሎት ፩ኛ ጢሞ ም ፪ ቁ ፪

፩ ለዓለም መንግሥታት ሰላምን ስጣቸው
ንዲተባበሩ እርስ በራሳቸው ።

፪ አንተ ለመረጥኸው ለሾምኸው ንጉሥ
ርሱ አታርቅበት የግርማን ሞገስ ።

፫ እሥራኤል ቢጠፉ አስነሣህ ሙሴን

ኢትዮጵያም ኃይለ ሥላሴን ።

፬ የግርማህን ብርሃን የሰጠህ ለሙሴ
ራም ስጥልን ለኃይለ ሥላሴ ።

፭ የኛ እቴጌ መነን ከቀኝ እንዳትጠፋ
ንለምንሃለን አምላክ የኛ ተስፋ ።

፮ ለኖኅ የሰጠኸው ቃል ኪዳንህን በውነት
ልጅ ልጅ እንዲሆን መንግሥቱን አጽናለት ።

፯ ዓለም በያለበት ጸንቶ እንዲተዳደር
ንተ ገለጥለት የሰላምን ምሥጢር ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ለመኳንንትና ለመሳፍንትህ
ቅን ፍርድ እንዲፈርዱ ይሰጥ መንፈስህ ።

መዝሙር ፺ ፡

ስለ ሀገር

፩ የሀገር ጠባቂ አምላክ ሃሌ ሉያ
ሰላምን ስጥልን ለኢትዮጵያ
፪ ክፉ ቢያስቡባት በሀገራችን
አምላክ አንተ አለህት የጦር ኃይላችን ።
፫ ሀገርን መገብህት በዝናም አብቅለህ
ጊዜም ሳትለውጥ በፀሐይ አብስለህ ።
፬ ምስጋና ይድረስህ አምላክ የኛ ተስፋ
የሀገር ፀጥታ የድሆች ደገፉ ።
፭ በሀገር ቸነፈር ረሀብ ቢበዛ
አምላክ አንፈራም አንተ አለኸን ቤዛ ።
፮ እሥራኤል ተርበው ሳሉ በቀኖና
አዘነምህላቸው መና ከደመና ።
፯ የእሥራኤል አምላክ የእሥራኤል ጌታ
ሀገርን ጠብቃት ፈጥና እንዳትፈታ ።

መዝሙር ። ፺፩

ስለ ነቢያት ።

፩ ወደፊት ያለውን ገልጦ ለመናገር
አምላክ አልሰጠህም ከነቢያት በቀር ።



፪ እውነት ተናገሩ ነቢያት በስምህ
ለነሱ የላክኸው ይምጣልን መንፈስህ
፫ ያንጊዜም አንተ ነህ ዛሬም አንተ ነህ
መንፈስህን ላክልት ይናገር ሕዝብህ ።
፬ በነቢያት አድረህ ከተናገርኸው
ተጽፎ የማያልቅ ሰው መሆንህ ነው ።
፭ ልደትህን ነቢያት እንደተናገሩ
አሁንም መምጣትህን ሰዎች ይመስክሩ ።
፮ ላንተ እሚመሰክር ሰው አስነሣልን
ሁላችን ጠፉን እንደበግ በረርን
፯ እንግዲህ እናስብ አምላካችንን
በነቢያት አድሮ የነገረንን
፰ ነቢያት ነገሩን አስረዱን ቃሉን
ደግሞም እንጠይቅ ሐዋርያትን ።

መዝሙር ። ፺፪

ስለ ሐዋርያት ።

፩ ቤቱንና እርስቱን ጥሎ ሊከተልህ
ፀንቶ እንዲኖር አርገው እግዚአብሔር በስምህ ።
፪ እንጠይቅ ተነሡ ሐዋርያትን
አይተውታልና ሲያፈሰው ደሙን ።
፫ የሐዋርያት ቃል ለዓለም ደረሰ
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየገሠገሠ ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ ዛሬም እንለምን መንፈስ ቅዱስን
ቃልን ለሚመራ ለሚሆን ብርሃን ።
፭ ሐዋርያቶችህ ዓለምን ንቀው
ወድቀው ተገረፉ ለስምህ ብለው ።
፮ እንደነሱ አጽናልን የኛንም ልቡና
ለስምህ ተገርፈን እንድናገኝ ጤና ።
፯ ዓለም አሸነፈን ወደቅነ እንደረሳ
መንፈስህን ላክልን ከብራችን ይነሣ ።

መዝሙር ። ፵፫

ስለ ጻድቃን ።

፩ አምላክ እንደመረጥህ ጻድቃኖችህን
ለመንግሥተ ሰማይ አብቃው ሕዝብህን ።
፪ በጻድቃን ታወቀ የዓለም ከንቱነት
ጥለዋት ሲሄዱ ወአምላክ ቸርነት ።
፫ ልባችን አይጽና በሚቀረው ዓለም
ለእኛም እንደ ጻድቃን ተከፍታለች ገዳም ።
፬ ባንዲት ልመናቸው ጻድቃንን ስትሰማ
እኛንም አዳምጠን ላለን ወጨለማ ።
፭ ጻድቃን ወብርሃንህ ይመላለሳሉ
አምላክ እኛ ቀረን ተለየን ከሁሉ ።
፮ ቆዳ እየለበሱ ከገዳም ሲኖሩ
ከነሱ አልተለየም አምላካችን ፍቅሩ ።



፯ ወርቅ የለበሰና ያጌጠ ፍጡር
ብሩ ሁሉ ቀረ ደረቀ እንደ ሣር
፰ (ይህን ተመልክቶ ይጠንቀቅ ፍጡር)

መዝሙር ። ፵፬

ስለ ሰማዕታት ።

፩ ደማቸው ፈሰሰ ወረደ እንደ ዝናም
ለቸር አምላካችን ለተቀደሰው ስም ።
፪ አምላክ ሰጠሃቸው የጽናትን መንፈስ
የወዳጆችህ ደም በስምህ እንዲፈስ ።
፫ ሰማዕታት ጽፈው ስምህን በደማቸው
ለኛ አስተላለፉት እንዳይሞት ስማቸው ።
፬ በደም የተጻፈው የኛ ሃይማኖት
ሲነበብ ይኖራል ቀንና ሌሊት ።
፭ በስም ክርስቲያን ሁነን እንዳንሞት
በሥራም ጨምረን እንደሰማዕታት ።
፮ አንገቱን ለሰለት ላዘጋጀልህ
ዘላለም የሚኖር ይምጣ መንግሥትህ ።
፯ እሱ ለፈጠረው ላዘጋጀው ሥጋ
በእሳት ወሰለት እንሙት ሳንሠጋ ።
፰ (ወዳገም ትንሣኤ እንድናገኝ ጸጋ)

www.ethiopianorthodox.org

## መዝሙር ፶፫

### ምሳሌ ማቴዎስ ።

ጸደይ ከመጋቢት ፳፮ እስከ ሰኔ ፳፭ (የበልግ ዘመን)

፩ አምላክ በምሳሌ ዘርን አሳየኸን
ፈርሶና በስብሶ ሲያወጣ ልምላሜን ።
፪ መሬት ተቀበለች ዘርዋን ከገበሬ
በአንተ ቸርነት እንድትሰጥ ፍሬ ።
፫ ሞት የሰው ገበሬ ዓለምን ቢዘራው
አምላክ ቸርነትህ ይታያል ሲያበቅለው ።
፬ በመንገድ ላይ ወድቆ ወፍ የበላው ዘር
አምላክ ጠብቀን ሁነን እንዳንቀር ።
፭ አንዲት ቅንጣት ፍሬ ስትበቅል በስብሳ
ሰው እንዴት ይቀራል ሙቶ ሳይነሣ ፣ ፧
፮ ሰው ከሞተ ወዲያ አይነሣም ሲሉ
አምላክ አስተማርኸው ዓለሙን በሙሉ ፣
፯ ሃሌ ሃሌ ሉያ ኃያል እግዚአብሔር
ትንሣኤን ሰጠኸን ሙተን እንዳንቀር
( ደግሞም አስረዳኸን በምሳሌ ዘር )

## መዝሙር ፶፬ ፣

### ምሳሌ ማርቆስ ፣

ክረምት ከሰኔ ፳፮ እስከ መስከረም ፳፭
የውሀ ዘመን)



፩ ዝናሙን በጊዜው ለሰጠነ ጌታ
እናቅርብ ምስጋና ጠዋትና ማታ
፪ ዝናምህን በጊዜው እንደሰጠኸን
እንዲሁም ምሕረትህ ፈጥና ይጎብኘን ፣

፫ ከበረድ አድነው የሕዝቡን አዝመራ
ረሃብ ነውና ትልቅ መከራ
፬ ከመከራ አድነን ከብዙም ችግር
የቸርነት አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ፣
፭ ለምድር ሰጠሀት ንጹሕ ዝናምን
ትቢያ ሆና እንዳትቀር ፍሬ እንድትሰጠን ፣
፮ ምድርን መገብሏን በሚያረካ ጠል
በረድና መብረቅ ሳትተላቀል ፣
፯ በብሩህ ደመና ሰማይን ሸፈንኸው
ደግሞም በልምላሜ ምድርህን ከደንኸው ።
( አምላክ ቸርነትህ ዘላለማዊ ነው)

## መዝሙር ፶፭

### ምሳሌ ሉቃስ ።

ጥቢ ( መጸው ) ከመስከረም ፳፮ እስከ ታኅሣሥ ፳፭

፩ የማይጨበጠው ረቂቅ ነፋስ
ለኛ ተዘጋጅ ሊሆነን መንፈስ ( ትንፋሽ )
፪ በነፋስ አደጉ ዕፀዋቱ ሁሉ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም አብበው አሁን ይታያሉ ፤
፫ አቤቱ ፍጥረትህ እንደምን ይረቃል
የገዘፈው ነገር በነፋስ ይሔዳል ።
፬ ሉቃስ ወንጌላዊ በነፋስ ሲመሰል
በውስጡ ይሰማል የመንፈስ ቅዱስ ቃል ፤
፭ ዛሬ ቢያስደስቱን አበቦች አብበው
ነገ ይታያሉ በእሳት ተጥለው ፤
፮ አምላክ ስንለምንህ ፈጥነህ አድምጠን
የአሁኑ ደስታ ኀዘን እንዳይሆን ፤
፯ ቀንሞስ አበበ ናርዶስ ጭምር
ዘመን ለመለየት ለመሆን ድንበር ።
( ምስጋና ይድረስህ ሕያው እግዚአብሔር )

መዝሙር ፶፯

ምሳሌ ዮሐንስ

ሐጋይ ( በጋ ) ከታህሣሥ ፳፮ እስከ መጋቢት ፳፭ ፤
፩ በለስ ለመለመች መከርም ደረሰ
የሰውም ዘመኑ ሄደ ገሠገሠ ።
፪ ሁልጊዜ ይሰማል ቃል ከዮሐንስ
ዓለሙን ለማዳን ሥጋ በመልበስ ፤
፫ ዮሐንስ ሲናገር የቃልን ነገር
ሕዝቡ ያስተውለው በልቡ ይደር
፬ ምሳሌህ ደረሰ አምላክ ምሕረት
ገለባና ፍሬው የሚለይበት ፤



፭ ገለባም ይጣላል ፈጥኖ በእሳት
ፍሬ ግን ይገባል ከቅዱሳን ቤት
፮ ለአብርሃም ለይስሐቅ የሰጠኸውን ፤
ዛሬም ለሕዝቦችህ ስጠን ሕይወትን ፤

፬ቱ ወንጌላውያን ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ክፍለ ዘመናት ይመሰላሉ ፤

በጸደይ ( በዘርዕ ወራት ) ማቴዎስ ።
በክረምት ( በውሀ ወራት ) ማርቆስ ።
በመፀው ( በነፋስ ወራት ) ሉቃስ ።
በሐጋይ ( በእሳት ወራት ) ዮሐንስ ።

አ ስ ረ ጅ ።

በጸደይ ማቴዎስ የተመሰለበት ምክንያት ከሁሉ ይልቅ ምሳሌ ዘርዕን አምልቶ አስፍቶ አብዝቶ ስለ ጻፈ ነው ። ዳግመኛም ወርኅ መሬት ነው ፤ እነሱውም ምድራዊ ልደቱን ጽፈዋልና ።

በክረምት ፤ ማርቆስ የተመሰለበት ምክንያት በጥምቀት ስለሚጀምር ነው ፤ ( ማር ም / ፩ )

በመፀው ሉቃስ የተመሰለበት ምክንያት በአምሳለ ነፋስ የሚሰጥ የመንፈስ ቅዱስን ነገር ( መንፈስቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ ) መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል የልዑልም ኃይል ይጸልል

www.ethiopianorthodox.org

ሻል እያለ ስለተናገረ ነው ( ሉቃስ ፩ ፴፰ ። )

<u>በሐዋይ ዮሐንስ</u> የተመሰለበት ምክንያት መስተፃርር መስተቃርን የሌለበት ደረቅ ቃል ( ቀዳሚሁ ቃል )ቃል አስ ቀድሞ ነበረ ብሎ ስለተፃገረ ነው ( ዮሐ ም ፩ ቍ ፩ ። )

<u>የዘወትር መዝሙር ፶፮ ።</u>

፩. በደምህ ተገዛ የጠፋው ዓለም
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፣ አምላክ ሰላም ።

፪. በደምህ አጠብኸው ኃጢአታችንን
ሃሌ ሃሌ ሉያ የዓለም መድኅን ።

፫. ሞቱህ ብትነሣ ፣ ደምህን አፍሰህ
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፣ ነው ላንተ ዋጋህ ።

※

፬. ፍርድህ አይረሳም ፣ ጠዋትና ማታ
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፣ የነገሥታት ጌታ ።


፭. ሕዝቦችህ ተነሡ ፣ አንተን ለማመስገን
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፣ አምላክ የኛ ብርሃን ።

፮, ወንዶችና ሴቶች ፣ ሕፃናቱ ሁሉ
ሃሌ ሃሌ ሃሌ ፣ ሃሌ ሉያ ፣ በሉ ።

※

፯, ፈጥኖ ስለሰጠን ፣ መንፈስ ቅዱስን
ሃሌ ሃሌ ሉያ ፣ እንበል ሁላችን ።

## በደምህ ተገዛ የጠፋው ዓለም ።






www.ethiopianorthodox.org

፳. በመንፈስ ይቀስቀስ ፡ አውታረ ልቡና
ይፀል ሃሌ ሉያ ፡ ይደርድር ምስጋና ።
፱ ሰላምን ለሰጠ ፡ ለኢትዮጵያ
በሉ ሃሌ ሃሌ ፡ ሃሌ ሃሌ ሉያ ።

※

የእግዚአብሔር ሕጐች በሚወዳቸው ፡
ላይ ይታያሉ ።

ቁ ፩ እንድታስደስተው እግዚአብሔር አምላክን ፡
በልብህ ጻፋቸው አሥሩ ቃላትን ።
፪ ማን ነገረኝ ብለህ ሀሳብ እንዳትፈጥር ፡
ተጽፈውልሃል በዚሁ መስመር ።

## ስለ ዐሠርቱ ቃላት ።

ትእዛዝ በጸሎት ጊዜ ቄሱ ዐሠርቱ ቃላትን እየለየና እያነበበ ለሕዝቡ ይንገራቸው ፤ በየቃላቱም መጨረሻ ሕዝቡ አቤቱ ይቅር በለን እያሉ የእግዚአብሔርን ጸጋ ይለምኑ ።

ይበል ካሕን ። እግዚአብሔር በደብረ ሲና ወርዶ በድንጊያ ጽፎ ለቀደሙ አባቶቻችን የሰጣቸው ዐሥርቱ ቃላት ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

## መጀመሪያ ትእዛዝ ።

እኔ እግዚብአሔር አምላክህ ነኝ .... ሌሎች አማልክት በፊቴ አይሁኑልህ ( አታምልክ ) ሥዕልንም

www.ethiopianorthodox.org

ምሳሌንም ከቶ ላንተ አታድርግ ። በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው በውሀም ከምድር በታች ካለው አትስገድላቸው አታምልካቸው እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክህ ነኝና ።(ዘፀአት ፳ ፪ ፯ ።)

ይበል ሕዝብ አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችንም ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## ሁለተኛ ትእዛዝ ።

ይ ፡ ካ ፡ የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው ( በከንቱ ስሙን አትጥራ ) እግዚአብሔር ስሙን ከንቱ ያደረገውን ሳይቀስፈው አይተወውምና (ዘፀአት ፳ ፯)

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## ሦስተኛ ትእዛዝ ።

ይ ፡ ካ፡ የሰንበትን ቀን አስብ ትቀድሰው ዘንድ ስድስት ቀን ሥራህን ሁሉ አድርግ ፤ ሰባተኛው ቀን ግን የእግዚአብሔር የአምላክህ ሰንበት ነውና በርሱ ሥራህን ሁሉ አትሥራ አንተ ወንድ ልጅህ ፡ ሴት ልጅህ ፡ አሽከርፀና ገረድህ ፡ ከብትህም ፡ በደጅህም የሚኖር እንግዳ ስደተኛ ይረፉ (ዘፀአት ፳ ፰ ፲፩ ።)

ይ ሕ አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ። (ዘፀአት ፳ ፲፪)



## አራተኛ ትእዛዝ ።

ይ ፡ ካ ፡ አባትህንና እናትህን አክብር እግዚአብሔር አምላክህ በሚሰጥህ ምድር ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ ።

ይ ፡ ሕ ፡ አቤቱ ይቅር፡ በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## አምስተኛ ትእዛዝ ።

ይ. ካ. አትግደል (ዘፀዓት ፳ ፲፫)

ይ ሕ አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## ስድስተኛ ትእዛዝ ።

ይ. ካ. አታመንዝር ። (ዘፀዓት ፳ ፲፬)

ይ. ሕ. አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን።

## ሰባተኛ ትእዛዝ ።

ይ ካ አትስረቅ (ዘፀዓት ፳ ፲፭ ።)

ይ ሕ አቤቱ ይቅር በለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

www.ethiopianorthodox.org

## ስምንተኛ ትእዛዝ ።

ይ. ካ. በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር (ዘፀ ፳ ፲፮ ። )

ይ. ሕ. አቤቱ ይቅር ባለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## ዘጠነኛ ትእዛዝ ።

ይ. ካ. የባልንጀራህን ቤቱንም ሚስቱንም አሽከሩም ገረዱንም በሬውንና አህያውንም ሌላውንም ከባልንጀራህ ገንዘብ ማናቸውንም ቢሆን አትመኝ (ዘፀአት ፳-፲፯ ።)

ይ. ሕ. አቤቱ ይቅር ባለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

## አሥረኛ ትእዛዝ ።

ይ. ካ. ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ (ዘሌዋ ፲፱፲፰)

ይ. ሕ. አቤቱ ይቅር ባለን ሰማያዊ አባታችን ሆይ ይህችን ትእዛዝህን በልባችን አሳድርብን ።

---

## ስለ ፮ቱ ቃላተ ወንጌል

በማቴዎስ ወንጌል በ፭ኛው ምዕራፍ የተጻፉት ፮ቱ ቃላት በጭሩ ። ፩ኛ በወንድሙ ላይ በከንቱ የተቆጣ ሁሉ



በፍርድ ይፈረድበታል ። ወንድሙን ግን ጨርቅ ለባሽ የሚለው በሸንጐ ይፈረድበታል ። ደንቆሮም የሚለው በገሃነመ እሳት ይፈረድበታል (ማቴ ፭ ፳፪)

፪ኛ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም በልቡ አመነዘረባት ማቴ ፭ ፳፰

፫ኛ ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የፈታ ሁሉ እርሱ አመንዝራ አደረጋት ፣ የተፈታችውንም ያገባ አመነዘረ (ማቴ ፭ ፴፪

፬ኛ ከቶ አትማሉ በሰማይስ እንኳን የእግዚአብሔር ዙፋን ትናና ፣ በምድርም የእግሩ ጫማ ናትና ፣ በኢየሩሳሌምም፣ የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፣ በራስህም አትማል፣ ከራስህ ጠጉር አንዲቱን ስንኳ ነጭ ወይም ጥቁር ታደርግ ዘንድ አትችልምና ።

ነገራችሁ ግን እንዲሁ ይሁን አዎን አዎን እንኳን እንኳን ከለዚህ የወጣ ግን ከክፉ የተገኘ ነው ማቴ ፭ ፴፬ ፴፯

፭ኛ ክፉውን በክፉ አትቃወሙት ። ማቴ ፭ ፴፱

፮ኛ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙዋችሁን ባርኩ ለሚጠሏችሁም መልካም አድርጉ ስለሚበድሏችሁም ስለሚያሳድዷችሁም ጸልዩ ማቴ ፭ ፵፬ ከዚህ በላይ የተጻፉት ትእዛዛት ግርማዊ ቀ - ኃ . ሥ .ንጉ ነገ ዘኢ ካሳተሙት የጸሎት መጽሐፍ የተቀዳ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## አባታችን ሆይ !

በሰማይ የምትኖር፣ስምህ ይቀደስ፡መንግሥትህ ትምጣ፡ ፈቃድህ በሰማይ እንደነሆች፡ እንዲሁም በምድር ትሁን ፣ የዕለት ምግባችንን ሰጠን ዛሬ፡ በደላችንን ይቅር በለን ፡ እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል ወደ ፈተናም አታግባን ፡ ከክፉ ሁሉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናትና ፤ ኃይል ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን ።

## እመቤታችን ድንግል ማርያም ሆይ !

በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እንልሻለን ፡ በሀሳብሽ ድንግል ነሽ ፣ በሥጋሽም ድንግል ነሽ ፣ የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ! ምሥጋና ላንቺ ይገባል ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ ፣ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ፤ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ፡ ጸጋን የተመላሽ ሆይ ! ደስ ይበልሽ፣እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነውና ፣ ከተወደደው ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታን ለምኝልን ፣ ኃጢአታችንን ፣ ያስተሠርይልን ዘንድ ፣ ለዘዓለሙ አሜን ።

### መዝሙር ፶፫

( ማቴዎስ ምዕራፍ ፮ ቍጥር ፱ )

፩ አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ
መንግሥትህ ትምጣልን ክብርህን እንድናይ ።

፪ ፈቃድህ በሰማይ ሕይወት እንደ ሆነ
እንዲሁም በምድር ሰላምን ስጠነ ።

## አባታችን ሆይ ፡፡






www.ethiopianorthodox.org

፫ ስጠነ ለዛሬ የዕለት ምግባችንን
በደላችንንም ይቅር እንድትለን ።

፬ ጌታ ሆይ አታግባን ከክፉ ፈታና
አንተ ካልረዳኸን ኃይል የለንምና

፭ ኃይልና ምስጋና መንግሥትም ያንተ ናት
አሜን ለዘለዓለም ይሁንልን ዕረፍት ።

## መዝሙር ፵፪

## የገብርኤል ብሥራት ፡

፩ ናዝሬት በምትባል ወዳንዲት አገር ሉቃ ፩ ቁ ፳፮
ገብርኤል ተላከ ድንግልን ሊያበሥር ።

፪ መልአኩም ወደሷ ገብቶ ሊጠይቃት ቁ ፳፰
ጸጋን የተመላሽ ደስ ይበልሽ አላት ።

፫ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋራ ነው ፫ እምላክ በጥበቡ አንቺን ስላነፃሽ
ከሴቶቹ ሁሉ የተባረክሽ ነሽ ።

፬ እሷም በነገሩ በጣም ደነገጠች ቁ ፳፱
እንዲህ ያል ሰላምታ ምንድርነው ? እያለች ።

፭ መልአኩም መለሰ አላት ማርያምን ቁ ፴
አትፍሪ አግኝተሻል ከእግዚአብሔር ዘንድ ጸጋን

፮ እነሆ ወንድ ልጅ ድንግል ትጸንሻለሽ ቁ ፴፩
ኢየሱስም ብለሽ ትሰይሚዋለሽ ።

፯ ይህ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅ ሲባል ቁ ፴፪
የዳዊትም ዙፋን ለሱ ይሰጠዋል ።

፳ ዘላለም ይነግሣል በያዕቆብ ቤት ቁ ፴፫
ፍጻሜ ሳይኖረው ለያዘው መንግሥት ።

ክፍል

፩ ወንድ ሳላውቅ እኔ ይህ እንዴት ይሆናል ቁ ፴፬
የሚል መልስ አገኘ መላኩ ከድንግል ።

፪ መላኩም መልሶ አላት ማርያምን ቁ ፴፭
ወዳንቺ ይመጣል መንፈስ ቅዱስ አሁን ።

፫ ደግሞም የልዑል ኃይል ይጸልልሻል
የሚወለደውም ቅዱስ ነው ኃያል ።

፬ በረቂቁ መልአክ የተመሰገንሽ
ምስጋና አቅርበናል እኛም ለክብርሽ ።

፭ ገነት ተዘግቶብን ሳለ በሔዋን
በድንግል ማርያም ተከፈተልን ።

፮ ዓለም እንዳይጠፋ አምላክ ተመልክቶ
ከድንግል አደረ ሥጋዋን አንፅቶ ።

፯ ሃሌ ሃሌ ሉያ አምላከ ሰላም (ሃሌ ዓለም ሳይፈጠር የነበርህ)
ባንተ ሥጋ መልበስ ጠፋ ገሃነም (ሉያ ዓለምን አሳልፈህ የምትኖር አምላክ)

ማሳሰቢያ ።

የሙዚቃ (የመዝሙር መጽሐፍ) ።

፬ት አስፈጊ የሆኑ ሀሳቦች አሉት ።

፩ኛ. ግጥሙን ለዜማ እንዲስማማ አድርጐ መድረስ።
፪ኛ. ለግጥሙ ድምፅ (ዜማ) መስጠት ፣



፫ኛ. በመሰንቆ አርጋኖ (ኖት) ባላቸው መሣሪያዎች ማስማማት ።
፬ኛ. ምልክት (ኖት) በተወሰኑት አምስት መስመሮች መጻፍ ናቸው ።

እነዚህን ሀሳቦች ተመልክተን ከዚህ ዓለም «የእንግድነት ዘመናችን» ሳይፈጸም ብንሠራባቸው ለሠራተኞች ስም ፣ ለሀገርም ኩራት ከመሆኑ በላይ የሰውን ልቡናደወ እግዚአብሔር ይመራሉ ። ደግቸውም በትዕቢት የፈላውን ያበርዳሉ የተኛውንም ህሊና ይቀሰቅሳሉ ።

እኔም እነዚህን ሀሳቦች በመከታተል በአዲስ አበባ ት/ ቤቶች እየተዘዋወርሁ በማስተምርበት ጊዜ ከባድና ረቂቅ የሆነው መንፈሳዊ ትምህርት በዚህ መስመር ቢመራ ሕፃናት በደስታ እንደሚቀበሉት ተገንዝቤ በ፲፱፻፷፯ ዓ ም በመጀመሪያ የታተመውን ፫ት ሺ (3000) መዝሙረ ጸሎት መጽሐፍ ለአዲሰ አበባ ት. ቤቶችና እንዲሁም ለየጠቅላይ ግዛቶቹ ት. ቤቶች በነፃ አበርክቻለሁ ።

ወደፊት ፫ኛ በሚቀጥለው መጽሐፍ የሀገርን ልማድና ባህል ሳይለቅ ለሕፃናት በቀላል ዜማ $^{2}/_{4}$
ለመካከለኛ ወጣቶች ባልረዘመ (ባላጠረ) ዜማ $^{3}/_{4}$
በዜማው ለሠለጠኑ ወጣቶች ግን $^{4}/_{4}$ (በረዥሙ) እንዲሆን በድርሯት ላይ እገኛለሁ ።

ከዚህ በላይ ግን ከባድ የሆነውን ምልክት (ኖት) በመጻፍ ስለረዱኝ አቶ ጸጋዬ ደባልቄን እያመሰገንሁ

www.ethiopianorthodox.org

በምክርና በማጽናናት ለረዳችሁኝ ሁሉ ልባዊ የሆነ ምስ ጋና አቀርባለሁ ።

ኢ.ሳ. ዓ ።

ምክር ሠናይት ለኩሉ ዘይገብራ ።

እውነትን ለመሰወር ናላህን አታዟረው መገለጡ አይቀርምና ።

※

ባለ ጸጋ ብትሆን አትደሰት ፣ ደሀም ብትሆን አት ዘን ፣ የማያልፍ ነገር የለምና ።

※

ባለሥልጣንና እሳት አንድ ናቸውና ሳይቀርቡም ሳይርቁም ነው ።

※

በተሾምህ ጊዜ ተመልካች እንደተሾመብህ ዕወቅ ።

※

ጠይቀህ መልስ ባጣህ ጊዜ ከባድ መልስ እንደተ መለሰልህ ዕወቅ እንጂ በከንቱ አትድከም ።

※

ጊዜ ቢያነግሀ አትደሰት ፣ ጊዜ ይጥልሃልና ፣ ጊዜም ቢጥልህ አትዘን ጊዜ ያነግሃልና ።


※

በደስታ ለመኖር ብትፈልግ በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አትመካ ። የማይሞት የማይሻር እግዚአብሔር ነውና ።

## ምስባክ፡

ምሩ፡ለአምላክነ፡ዘምሩ፡ዘምሩ፡ለንጉሥነ፡ዘምሩ።

ስመ፡ንጉሥ፡እግዚአብሔር፡ለኩሉ፡ምድር።






www.ethiopianorthodox.org

| ቍጥር | ማውጫ ። | ገጽ |
|---|---|---|
| | መቅድም | ፰ |
| | የመዝሙረ ጸሎት ጥቅሶች ፣ | ፱ |
| | የጳውሎስ መልእክት ፣ | ፲ |
| ፩ | ስለ ርእሰ ዓውደ ዓመት ፣ | ፲፬ |
| ፪ | ዘመስቀል ፣ | ፲፭ |
| ፫ | ዘመነ ጽጌ ፣ | ፲፮ |
| ፬ | ልደተ ክርስቶስ ፣ | ፲፯ |
| ፭ | ጥምቀት በዮርዳኖስ ፣ | ፲፰ |
| ፮ | የክርስቶስ ጾምና ፈተና ፣ | ፲፱ |
| ፯ | ሕይወት በመጻጕዕ ፣ | ፳ |
| ፰ | ሐዋዊ መሢሕ በደብረ ዘይት ፣ | ፳፩ |
| ፱ | ሆሣዕና ለወልደ ዳዊት ርግመተ በለስ ፣ | ፳፪ |
| ፲ | ስቅለተ ክርስቶስ ፣ | ፳፫ |
| ፲፩ | ብርሃነ ትንሣኤ በክርስቶስ ፣ | ፳፬ |
| ፲፪ | ዳግም ትንሣኤ ፣ | ፳፭ |
| ፲፫ | ዕርገተ ክርስቶስ ፣ | ፳፮ |
| ፲፬ | ጰራቅሊጦስ በጰንጠቈስጤ ፣ | ፳፯ |
| ፲፭ | ብርሃነ መለኮት በደብረ ታቦር ፣ | ፳፰ |
| ፲፮ | ማኅበራዊ ጸሎት ፣ | ፴ |
| ፲፯ | ከሙቶ ፴ መዝሙረ ዳዊት ፣ | ፴፩ |
| ፲፰ | ፳፯ መዝሙር ዳዊት የሚለው ፣ | ፴፪ |
| ፲፱ | አቤቱ በስምህ አድነኝ ፣ | ፴፫ |

www.ethiopianorthodox.org

| ቁጥር | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፳ | እንደቸርነትህ ፣ | ፸፫ |
| | ክፍል ፣ | ፸፬ |
| ፳፩ | አቤቱ አባት ሆይ ፣ | ፸፭ |
| ፳፪ | ያዘነ መንፈስ ፣ (፶፪ን ፪፱ በል) | » |
| ፳፫ | አንተ ትነሣለህ ፣ | ፸፯ |
| ፳፬ | እግዚአብሔርን ባርኪ ነፍሴ ፣ | ፸፯ |
| ፳፭ | የዓለም ከንቱነት ፣ | ፸፰ |
| ፳፮ | አቤቱ አምላኪየ ፣ | ፸፱ |
| ፳፯ | አቤቱ በጽዮን | ፹ |
| ፳፰ | ቃሌን አድምጥልኝ ፣ | ፹፩ |
| ፳፱ | ሕጉን የሚያነቡ ፣ | ፹፪ |
| ፴ | የሐና ጸሎት ፣ | ፹፫ |
| | ክፍል ፣ | ፹፬ |
| ፴፩ | ሃሌ ፣ ሃሌ ሉያ ፣ እግዚአብሐር ፈጣሪ ፣ | » |
| ፴፪ | የእግዚአብሐርን ስሙን አመስግኑ ፣ | ፹፭ |
| ፴፫ | እግዚአብሔር ነገሠ ፣ | ፹፮ |
| ፴፬ | ከኔ እንድታርቀው ፣ | » |
| ፴፭ | አቤቱ እስከ መቼ ትረሣኛለህ ፣ | ፹፯ |
| ፴፮ | እንደ ዓይን ብሌኔ ፣ | ፹፰ |
| ፴፯ | ሃሌ ሃሌ ሉያ እሱን አመስግኑት ፣ | » |
| ፴፰ | የኤልያስ አምላክ ፣ | ፹፱ |
| ፴፱ | ስለ ንጉሥ ጸሎት ፣ | ፺ |
| ፵ | ስለ ሀገር ፣ | ፺፩ |



| ቁጥር | ማውጫ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፵፩ | ስለ ነቢያት ፣ | ፺፩ |
| ፵፪ | ስለ ሐዋርያት ፣ | ፺፪ |
| ፵፫ | ስለ ጻድቃን ፣ | ፺፫ |
| ፵፬ | ስለ ሰማዕታት ፣ | ፺፬ |
| | **ክፍለ ዘመናት ፣** | |
| ፵፭ | ጸደይ ( የበልግ ዘመን ) ምሳሌ ማቴዎስ ፣ | ፺፭ |
| ፵፪ | ክረምት ( የውሀ ዘመን ) ማርቆስ } ቁጥሩ የተደጋገመ | » |
| ፵፭ | ጥቢ ( መፀው )» ሉቃስ | ፺፮ |
| ፵፯ | ሐጋይ በጋ) » ዮሐንስ | ፺፯ |
| | ስለ ፬ቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ፣ | ፺፰ |
| ፵፮ | በደምህ ተገዛ የጠፋው ዓለም ፣ | ፺፱ |
| | ስለ አሥርቱ ቃላት ፣ | ፻ |
| | ስለ ፯ቱ ቃላተ ወንጌል ፣ | ፻፫ |
| ፵፰ | አባታችን ሆይ ! | ፻፭ |
| ፵፱ | የገብርኤል ብሥራት | ፻፯ |


ከዚህ በላይ የተጠቀሱት መዝሙሮች ከምስባኩ ምልክት ( ኖት ) በቀር በድምፅ ይወራረሳሉ ።

ያንዱ ዜማ( ላንዱ ይሆናል )

ከዚህ በላይ ግን ጠቅላላውን መጽሐፉ ከብሉይና ከሐዲስ የተጠቀሰ ስለሆነ አንባቢው ወይም ዘማሪው ምዕራፉንና ቁጥሩን እየተከታተለ የተሳሳተ ቢኖር ከብሉይና ከሐዲስ ሊረዳው ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org